የመጀመሪያ ዙር የአ-ክፍል ትምህርት ኢንስፔክሽን ውጤት ትንተና

አጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን

ታህሳስ 07, 2015

ትምህርት ሚኒስቴር

ማውጫ

ምስጋና iv

መልዕክት v

አጭር ማጠቃለያ x

1. መግቢያ 1

2. ዓላማ 2

2.1 ዋና ዓላማ 2

2.2 ዝርዝር ዓላማ 2

2.3 አስፈላጊነት 2

3. የኦ-ክፍል ደረጃ ምደባ 3

4. የመረጃ አሰባሰብና ትንተና ሂደት 4

4.1 የመረጃ አሰባሰብ 4

4.2 የትንተና ዘዴዎች 4

5. የመጀመሪያው ዙር የኦ-ክፍል ኢንስፔክሽን 5

5.1 የኦ-ክፍል ትምህርት ኢንስፔክሽን አገልግሎት ስርጭት 6

5.2 የክልሎች ኦ-ክፍል ኢንስፔክሽን አፈፃፀም በደረጃ 7

5.3 የክልሎች ኦ-ክፍል ኢንስፔክሽን አፈፃፀም በደረጃ በከተማና በገጠር 7

5.3.1 ኦ-ክፍል ኢንስፔክሽን አፈፃፀም በደረጃ በከተማ 7

5.3.2 ኦ-ክፍል ኢንስፔክሽን አፈፃፀም በደረጃ በገጠር 9

5.3.3 ኦ-ክፍል ኢንስፔክሽን አፈፃፀም ሀገር አቀፉ ከከተማ ንፅፅር 11

5.4 የኦ-ክፍል ኢንስፔክሽን አፈፃፀም በትኩረት መስኮችና በደረጃ 12

5.4.1 የኦ-ክፍል ትምህርት ኢንስፔክሽን አማካኝ አፈፃፀም በክልል 12

5.4.2 የኦ-ክፍል ኢንስፔክሽን አፈፃፀም በግብዓት የትኩረት መስኮችና በደረጃ 13

5.4.3 የኦ-ክፍል ኢንስፔክሽን አፈፃፀም በሂደት የትኩረት መስኮችና በደረጃ 14

5.4.4 የኦ-ክፍል ኢንስፔክሽን አፈፃፀም በውጤት የትኩረት መስኮችና በደረጃ 15

6. ከ2012-2014 ዓ.ም የተከናወነው የኦ-ክፍል ኢንስፔክሽን አፈፃፀም በትኩረት መስኮች 16

6.1 የትምህርት ፋሲሊቲ፣ ህንፃዎች 16

6.2 የሰው ኃይል 17

6.3 የገንዘብ ምንጮች 18

6.4 ምቹ የመማሪያ አካባቢና የምድረ ግቢ ገጽታ 19

6.5 መማር እና እንክብካቤ 20
6.6 ማስተማር 20
6.7 ርዕሰ መምህሩ (አስተባባሪ) 21
6.8 የኦ-ክፍሉ ማህበረሰብና የህፃናት ግንኙነት 22
6.9 የስርዓተ ትምህርት አተገባበርና ምዘና 23
6.10 የትምህርት ቤት፣ የወላጆች/አሳዳጊዎችና የማህበረሰብ አጋርነት 25
6.11 የህፃናት ተሳትፎ እና የውስጥ ብቃት 26
6.12 የህፃናት ግለ-ስብዕና 27
6.13 የመምህራንና የርዕሰ መምህር/አስተባባሪ ግለ - ስብዕና 28
6.14 የወላጆችና የአካባቢው ማህበረሰብ ተሳትፎ 29
7. ምዕራፍ አንድ እና ምዕራፍ ሁለት 30
7.1.1 ምዕራፍ አንድ ኦ-ክፍሎች የ2012 ዓ.ም ኢንስፔክሽን በክልል እና በደረጃ 31
7.1.2 ምዕራፍ አንድ ኦ-ክፍሎች የ2013 ኢንስፔክሽን በክልል አፈፃፀም በደረጃ 32
7.1.3 ምዕራፍ አንድ ኦ-ክፍሎች የ2014 ዓ.ም ኢንስፔክሽን በክልል እና በደረጃ 33
7.2 ምዕራፍ ሁለት ኦ ክፍሎች ኢንስፔክሽን 34
8. መደምደሚያ 35
9. ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫ 37
ተቀፅላ 39

ሠንጠረዥ

ሠንጠረዥ ፡ 1. የመለኪያዎችና የስታንዳርዶች ትስስር 3
ሠንጠረዥ ፡ 2. ከ2012-2014 ዓ.ም የተከናወነ የኦ-ክፍል ኢንስፔክሽን አፈፃፀም በደረጃ 5
ሠንጠረዥ ፡ 3.በከተማ የሚገኙ የኦ-ክፍል ኢንስፔክሽን አፈፃፀም ደረጃ በክልል 7
ሠንጠረዥ ፡ 4.በገጠር የሚገኙ የኦ-ክፍል ኢንስፔክሽን አፈፃፀም ደረጃ በክልል 9
ሠንጠረዥ ፡ 5.ምዕራፍ አንድ የ2012 ዓ.ም ኢንስፔክሽን በክልል እና በደረጃ 31
ሠንጠረዥ ፡ 6.የምዕራፍ አንድ ኦ-ክፍሎች ኢንስፔክሽን ዕቅድ፣ የክልሎች አፈፃፀም በደረጃ 32
ሠንጠረዥ ፡ 7. ምዕራፍ አንድ ኦ ክፍሎች የ2014 ዓ.ም ኢንስፔክሽን በክልል እና በደረጃ 33
ሠንጠረዥ ፡ 8.ምዕራፍ ሁለት ኦ-ክፍል የመጀመሪያ ዙር ኢንስፔክሽን በደረጃ 34

ግራፍ

ግራፍ 1. የኦ-ክፍሎች ኢንስፔክሽን አፈፃፀም ደረጃ በክልል 7
ግራፍ 2. በክልሎች የገጠርና ከተማ ኦ-ክፍል ኢንስፔክሽን አፈፃፀም በደረጃ 8
ግራፍ 3. የከተማና የገጠር ከሀገር አቀፉ አማካይ አፈፃፀም ንፅፅር በትኩረት መስኮች 11
ግራፍ 4. የኦ-ክፍሎች ኢንስፔክሽን አፈፃፀም በግብዓት ትኩረት መስኮችና በደረጃ 13
ግራፍ 5. የኦ-ክፍሎች ኢንስፔክሽን አፈፃፀም በሂደት የትኩረት መስኮችና በደረጃ 14
ግራፍ 6. የኦ-ክፍሎች ኢንስፔክሽን አፈፃፀም በውጤት የትኩረት መስኮችና በደረጃ 15
ግራፍ 7. የትምህርት ፋሲሊቲ፣ ህንፃዎች 16
ግራፍ 8 .የሰው ኃይል 17
ግራፍ 9. የገንዘብ ምንጮች 18
ግራፍ 10. ምቹ የመማሪያ አካባቢና የምድረ ግቢ ገጽታ 19
ግራፍ 11 .መማር እና እንክብካቤ 20
ግራፍ 12. ማስተማር 20
ግራፍ 13. ርዕሰ መምህሩ(አስተባባሪ) 21
ግራፍ 14. የት/ቤቱ ማህበረሰብና የህፃናት ግንኙነት 22
ግራፍ 15. የስርዓተ ትምህርት አተገባበርና ምዘና 23
ግራፍ 16. የትምህርት ቤት፣ የወላጆች/አሳዳጊዎችና የማህበረሰብ አጋርነት 25
ግራፍ 17. የህፃናት ተሳትፎ እና የውስጥ ብቃት 26
ግራፍ 18. የህፃናት ግለ-ስብዕና 27
ግራፍ 19. የመምህራንና የርዕሰ መምህር/አስተባባሪ ግለ - ስብዕና 28
ግራፍ 20. የወላጆችና የአካባቢው ማህበረሰብ ተሳትፎ 29

ምስጋና

በዚህ ሀገር አቀፍ የአጠቃላይ ትምህርት የኦ-ክፍል ኢንስፔክሽን ትንተና ለሁሉም ባለድርሻ አካላት ለአገልግሎት እንዲበቃ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በርካታ አካላት ተሳትፎ አድርገዋል። በመጀመሪያ ምስጋና የሚገባቸው የአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ የሆኑት ዶክተር ፋንታ ማንደፍሮ፣ የአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን ዴስክ ኃላፊ የሆኑትን አቶ አስፋው መኮንን ይህ ሪፖርት ተተንትኖ ለዚህ እንዲበቃ በቅርበት በመከታተል ያላሰለሰ ድጋፍ ያደረጉ መሆናቸውን ማስታወስ ያስፈልጋል። በተጨማሪም ሊመሰገኑ የሚገባቸው የሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደር የአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን ዳይሬክተሮች የኦ-ክፍሎች ኢንስፔክሽን መረጃ ተሰብስቦ በወቅቱ ለአገልግሎት እንዲውል የበኩላቸውን አስተዋፅዎ አድርገዋል። በመጨረሻም ከፍተኛ ምስጋና የሚቸራቸው ይህ ትንተና ተፅፎ በማጠናቀቅ የተሳተፉ ለሁሉም የአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን ዴስክ ባለሙያዎች ጨምሮ የትንተናው ረቂቅ በማዘጋጀት ለዚህ እንዲበቃ ያደረጉት አቶ አላምረው አክሊሉ ከፍ ያለ ምስጋና ይቸራችኋል።



መልዕክት



የትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል ሥራ አስፈፃሚ

ለአንድ ሀገር ጥራት ያለው የትምህርት ልማት ስርዓት የላቀ ብቃት ያለው፣ ተወዳዳሪ የሆኑና የተሟላ ዕድገት ማምጣት የሚችሉ ዜጎችን ለመፍጠር የሚያስችል ቁልፍ መሳሪያ ሲሆን ለዘላቂ የልማት ግቦች ስኬት አዎንታዊ አስተዋጽኦ ያበረክታል። ይህንን እውነት በመገንዘብ ሀገራችን አሁን ያለውን የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ፣ የማህበራዊ እና የቴክኖሎጂ ልማት የሚመራ የሠው ኃይል የሚያወጣ ጥራት ያለው የትምህርት ስርዓት ለማሳደግ ጠንክራ እየሰራች ትገኛለች። ለዚህም በሀገር አቀፍ ደረጃ የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ መርሐ ግብር /GEQIP/ ተቀርፆ በመተግበር ላይ ይገኛል። በተለይም የትምህርት ስርዓቱን ለማሻሻል የተዘጋጀው ፍኖተ-ካርታ የትምህርት ተደራሽነትን ፣ ፍትሐዊነትን እና ተገቢነትን በማረጋገጥ የትምህርት ጥራት በማስፋፋት ላይ የበለጠ አፅንኦት ተሰጥቷል።

የአጠቃላይ ትምህርት ልማት ዘርፍ ፕሮግራምን ለማሳካት የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ መርሐ ግብር /GEQIP/ በ1999ዓ.ም ተቀርፆ ስራ ላይ ሲውል በተለይም በትምህርት ቤት መሻሻል መርሀ-ግብር ዕቅዶችን ለማሳካት በትኩረት ሲሰራበት ቆይቷል። የሰነዶች እና ስትራቴጂክ ዕቅዶች

መዘጋጀት ለትምህርት ጥራት መሻሻል ዋስትና ባይሆንም የትምህርት አቅርቦት በመላ ሀገሪቱ በተፋጠነ ሁኔታ ለመተግበር አስችሏል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ ለሁሉም ዜጎች ጥራት ያለው ትምህርት በፍትሐዊነት ለማቅረብ እንዲያስችል ዘላቂ የልማት ግቦች / SDGs/ ተቀርፆ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል። ለዚህም ሰኬት በየጊዜው በሁሉም ደረጃ የሚሰጠው ትምህርት ጥራትና ተገቢነት ያለው ሆኖ ከሀገሪቱ የዕድገት ደረጃ ጋር ተገናዝቦ እንዲሄድ በርካታ ጥረቶች እየተደረጉ ይገኛሉ።

ከነዚህም ጥረቶች መካከል ለቅድመ መደበኛ፣ ለመጀመሪያና መካከለኛ እና ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የኢንስፔክሽን አገልግሎት በመስጠት ት/ቤቶቹ በግብዓት፣ በሂደት እና በውጤት የአፈፃፀም መለኪያዎች ተገምግመው ደረጃ እየወጣላቸው ይገኛል።
በሀገራችን ለሚገኙ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት መስጫ (ኦ-ክፍል) ከ2012-2014ዓ.ም የመጀመሪያ ዙር የኢንስፔክሽን አገልግሎት ተሰጥቷቸዋል። ይህንን ተከትሎም የቅድመ አንደኛ ማዕከላቱ ጥንካሬና ድክመት ሊያሳይ የሚችል ዝርዝር የኢንስፔክሽን አፈፃፀም ሪፖርት ተዘጋጅቷል። እነዚህ ኦ-ክፍሎች ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት መሰረት የሚጣልባቸውና የሕፃናቱን ማህበራዊ፣ አካላዊና አእምሯዊ ዕድገቶች መሻሻላቸውን ክትትል የሚደረግበት በመሆኑ ልዩ ትኩረት የሚፈልጉ ናቸው። በመሆኑም ለቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ጥራት ላይ መሻሻል በተለይም ለህፃናቱ ቀጣይ የትምህርት ዕድገት ላይ ሊያደርስ የሚችለውን አሉታዊ ተጽዕኖ ለመቀነስ ብሎም ለመቅረፍ ሀብረተሰቡ ከመንግስት ጋር በመቀናጀት የድርሻቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል። የኢንስፔክሽን ሪፖርቱ በዚህ መልክ መዘጋጀቱ በሁሉም ደረጃ ለሚገኙ የትምህርት አመራሮች፣ የትምህርት ተቋማትና ባለድርሻ አካላት ተደራሽ ያደርገዋል። ስለሆነም ለትምህርት ጥራት መሻሻል አስተዋፅኦ እንዲኖረው ከትምህርት ሚኒስቴር እስከ ወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ድረስ የምትገኙ የኦ-ክፍል ኢንስፔክሽን አፈፃፀም ሂደት ላይ ተሳትፋችሁ የበኩላችሁን አስተዋፅኦ ያበረከታችሁ ለትምህርት ጥራት መሻሻል እያበረከታችሁ ያለውን አስተዋፅኦ ማመስገን እፈልጋለሁ። የትንተና ሪፖርቱም በቀጣይ በየደረጃው በሚገኙ አካላት የዕቅድ ግብዓት ሆኖ እንደሚያገለግል እና ለአፈፃፀሙም የአመራሩን ከፍተኛ ትኩረት ያገኛል የሚል እምነት አለኝ።

በየደረጃው የምትገኙ የትምህርት አመራሮች፣ መምህራን፣ የትምህርት ባለሙያዎች ፣ ወላጆችና ባለድርሻ አካላት የትምህርት ጥራት ማረጋገጥ ሥራችን የልጆቻችንን የወደፊትም ህይወት እና

የሀገራችንን የወደፊት ብልፅግና የሚወስን እና ሀገራችንን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ለማድረግ ጭምር ወሳኝ ሚና አለው።

ሀገራችን የጀመረቻቸውን ታላላቅ ሥራዎች ወደፊት እንዲቀጥሉ እና በሚሊዮኖች ለሚቆጠሩ ልጆቻችን የወደፊት ህይወታቸውን ብሩህ ለማድረግ የሁላችንም ርብርብ የሚፈልግና ሁላችንም የራሳችንን የጣት አሻራ በማኖር ሃላፊነታችንን እንድንወጣ በድጋሚ ላስታውስ እፈልጋለሁ።

አቶ ዮሐንስ ወጋሶ

የአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን ዴስክ ሃላፊ መልዕክት



በአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ በትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል መሪ ሰራ አስፈፃሚ ኢንስፔክሽን ዴስክ በሀገር አቀፍ ደረጃ የትምህርት ቤቶችን ኢንስፔክሽን ተግባራት ማከናወን ከጀመረ ዘጠኝ ዓመታትን ያሳለፈ ሲሆን ትምህርት ቤቶች ያለባቸውን ክፍተቶች በመለየት የአፈፃፀም ደረጃቸውን እንዲያሻሽሉ በየደረጃው ድጋፍና ክትትል እያደረገ ይገኛል።

የአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን ማዕቀፍ ትምህርት ቤቶችን በግብዓት፣ ሂደትና ውጤት ስታንዳርዶች በመገምገም የአፈፃፀም ደረጃ በማውጣትና በተለይ መሻሻል ባለባቸው ጉዳዮች ላይ የተመሰረተ ግብረ-መልስ በየደረጃው ለሚገኙ አካላት ይሰጣል።

ይህ የመጀመሪያው ዙር የኦ-ክፍል ትምህርት ኢንስፔክሽን አፈፃፀም ትንተና በዚህ መልክ ሲቀርብ ለትምህርት ጥራት መሻሻል በየደረጃው የሚገኙ አካላት ግብዓት እንደሚያገኙበት በማሰብ ነው። በሀገራችን የኦ-ክፍል ኢንስፔክሽን አገልግሎት ከ2012 ዓ.ም የትምህርት ዘመን ጀምሮ መስጠት የተጀመረ ሲሆን ከ2012-2014ዓ.ም ለ30,152 ለኦ-ክፍል ትምህርት መስጫ ማዕከላት የኢንስፔክሽን አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ16,377 አገልግሎቱን አግኝተዋል። አፈፃፀሙ 54.3% ሲሆን የቀነሰበት ዋነኛ ምክንያት በከተሞች የሚገኙት በህብረተሰብ ተሳትፎ ወደ አዕደ ሕፃናት እያደጉ ሲሆን ሌሎች ኦ-ክፍሎች ሲከፈቱ በህብረተሰቡ ፍላጎት መሰረት በመሆኑ እና በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፍላጎት መሰረት የሚከፈቱ በመሆኑ የነበራቸው ቁጥር እንዲቀንስ አስተዋፅዎ ነበረው።

የኡ-ክፍል ትምህርት መስጫ ማዕከላት ደረጃ ለማሻሻል በተለይም የግብዓት እና የሂደት ስታንዳርዶች ላይ ስራዎች ከተከናወኑ በቀላሉ የአፈፃፀም ደረጃቸው ሊሻሻል እንደሚችል የተለያዩ ተሞክሮዎችና ጥናቶች ያሳያሉ።

ከግብዓት ስታንዳርዶች በዋናነት የትምህርት ፋሲሊቲ፣ ህንፃዎች፣ የሰው ሀይል፣ የገንዘብ ምንጮች፣ ምቹ የመማሪያ አካባቢ ከመፍጠር አኳያ ይመዘኑበታል።

ከሂደት ስታንዳርዶች መማር እና ማስተማር፣ ማህበረሰብና የህፃናት ግንኙነት፣ የስርዓተ ትምህርት አተገባበር፣ ምዘና፣ የትምህርት ቤት፣ የወላጆች/አሳዳጊዎችና የማህበረሰብ አጋርነት፣ የሕፃናት ተሳትፎ እና የውስጥ ብቃት፣ የህፃናት ግለ-ስብዕና፣ የመምህራንና የርዕሰ መምህር/አስተባባሪ ግለ - ስብዕና በሚሉ የትኩረት መስኮች ብቃታቸው ተፈትሾ በማረጋገጥ ደረጃ ይወጣላቸዋል።

የኢንስፔክሽን ሪፖርት በተለይም በክልሎች፣ በገጠርና በከተማ፣ በትምህርት ቤት መሻሻል የትኩረት መስኮች መሰረት ተተንትኖ ቀርቧል።

በመሆኑም የዚህ ትንተና ሰነድ በየደረጃው የሚገኙ የትምህርት አመራሮችና ባለሙያዎች ፣ ባለድርሻ አካላት፣ ከፍተኛ አመራሮች፣ ፖሊሲ አውጪዎች፣ የመምህራን ትምህርት ኮሌጆችና በትምህርት ዘርፍ የተሰማሩ አጋሮች ለትምህርት ጥራት መሻሻል ለሚያደረጉት አስተዋፅዎ እንዲያግዝ ሆኖ ተዘጋጅቷል።

አቶ አስፋው መኮንን

አጭር ማጠቃለያ

የትምህርት ቤት ኢንስፔክሽን፣ ትምህርት ቤቶች የሚሰጡትን ትምህርት ከግብዓት፣ ከሂደትና ከውጤት አንጻር ያለውን ብቃትና ጥራት ለማረጋገጥ ነፃ በሆነ ውጫዊ አካል የሚካሄድ ግምገማ ነው። የትምህርት ቤት ኢንስፔክሽን አገልግሎት በግብዓት፣ በሂደትና በውጤት ላይ የተመረኮዙ 22 ስታንዳርዶችን መነሻ በማድረግ አንድን የኦ-ክፍል ኢንስፔክሽን ከሁለት እስከ ሶስት ቀናት የመገምገም ተግባር ነው። በሶስቱም መለኪያዎች (በግብዓት፣ ሂደትና ውጤት) ተገምግመው ያገኙት አማካይ ውጤት ከ50% በታች ከሆነ ደረጃ አንድ፣ ከ50%-69.99% ደረጃ ሁለት፣ ከ70%-89.99% ደረጃ ሶስት ፣ ከ90%-100% ደረጃ አራት ላይ ይመደባሉ። ደረጃ አንድ ላይ የሚያርፉ አፈጻጸማቸው በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ ይህን ውጤት ለማሻሻል ብዙ መስራት የሚጠበቅባቸው ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደረጃ አራት ላይ የሚያርፉ የላቀ አፈጻጸም ያላቸው በመሆኑ ለሌሎች ትምህርት ቤቶች ሞዴል ሆነው ሊያገለግሉ ይችላሉ ተብሎ ይታመናል።

የሰነዱ ዋነኛ ዓላማ ለትምህርት ቤቶች የሚሰጠው የኢንስፔክሽን አገልግሎት የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ ያለውን ሚና ለመለየት እንዲሁም ለትምህርት ቤቶች የአፈጻጸም ብቃት ላይ ያመጣውን ለውጥ ለመመርመር /ለመፈተሽ/ ነው።

የተሰጡ የኢንስፔክሽን አገልግሎቶች በወረዳ ኢንስፔክተሮች ሲሆን በየደረጃው የሚገኙ የዞን፣ የክልል እና የፌደራል አጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን ሥራ ክፍሎች አማካኝነት ከሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ወጥ በሆነ ቅፅ መረጃ የመሰብሰብ ስራዎችን አከናውኗል። የተሰበሰቡት መረጃዎች ትኩረት ያደረጉት በግብዓት፣ በሂደትና በውጤት ስታንዳርዶች ሲሆኑ በየክልል፣ በዞን፣ በወረዳ፣ በክተማ፣ በገጠር፣ የመንግስት/የግል የኢንስፔክሽኑ አካል፣ ኢንስፔክሽኑ የወሰደበት ጊዜን፣ ሲሆን ለመለያነት ኦ-ክፍል ትምህርት የሚሰጥበትን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት መለያ ኮድ ጥቅም ላይ ውሏል።

ይህ የመጀመሪያ ዙር የኦ-ክፍል ትምህርት ኢንስፔክሽን ከ2012-2014ዓ.ም የተከናወነ ሲሆን ለ16,377 አገልግሎቱ ተሰጥቷል። አፈፃፀሙን ስንመለከት 10,538 (64.3%) ደረጃ አንድ ፣ 5,623 (34.3%) ደረጃ ሁለት ሲሆኑ ስታንዳርዱን ያሟሉት 216 (1.3%) ብቻ ናቸው። ይህ የሚያሳየው መንግስት እና ህብረተሰቡ ለቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት አገልግሎት የተሰጠው ትኩረት አነስተኛ መሆኑን ሲሆን በቀጣይ የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ የሚጠይቅ ይሆናል።

ጉዳዩ የፍትሐዊነት ጥያቄ ውስጥ የሚያስገቡ ጉዳዮችንም የያዘ በመሆኑ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት መሰጫ አካባቢዎችን ምቹ በማድረግና በቂ የሰለጠኑ መምህራን አቅርቦት የሚጠይቅ በመሆኑ የኢጋሮችንና ባለድርሻ አካላትንም ተሳትፎ ይጠይቃል። የትንተና ሪፖርቱ እንደሚጠቁመው ለኦ-ክፍሎች ለደረጃው የሚመጥኑ ብቃት ያላቸው አስተባባሪዎች፣ ለደረጃው የሚመጥኑ መምህራን፣ የገንዘብ እና የንብረት ሃብት አጠቃቀም ስርዓት ዘርግቶ በመተገብር እና የሕፃናትና ኦ-ክፍል የህብረተሰብ ኢጋርነት፣ የሥርዓተ ትምህርት አተገባበሩ ዙሪያ በርካታ ቀሪ ስራዎች መኖራቸውን ከትንተናው መረዳት ተችሏል።

በተመሳሳይ የትምህርት ፍኖተ-ካርታው የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ተደራሽነትን አስመልክቶ ከሌሎች ሀገሮች ጋር ሲነጻጸር ዝቅተኛ አፈጻጸም እንዳለ ከማመልከቱ በተጨማሪ፣ በትምህርት ዘርፉ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ዋነኛ የትኩረት ጉዳይ በመሆኑ ከፍተኛ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል። ለዚህም የብቃት ደረጃ ላይ መድረሳቸውን ለማረጋገጥ የተጠናከረና ተከታታይነት ያለው ክትትልና ግምገማ እንዲካሄድ እንዲሁም መንግሥትና በትምህርት ዘርፍ የሚሠሩ አጋር ድርጅቶች ድጋፋቸውን አጠናክረው በመቀጠልና ቀጣይነት ያለው ክትትል በማድረግ ደረጃ-1 እና ደረጃ-2 ላይ የሚገኙ ኡ-ክፍል ትምህርት ብዛት ለመቀነስ ትኩረት ሰጥተው ማከናወን ይጠበቅባቸዋል።

1. መግቢያ

የትምህርት ቤት ኢንስፔክሽን አገልግሎት ትምህርት ቤቱ ምቹ የመማሪያ አካባቢ ስለመፍጠሩና ጥራት ያለው ትምህርት ስለመሰጠቱ በግብዓት፣ ሂደትና ውጤት ስታንዳርዶች ተገምግመው የሚረጋገጥበት ሂደት ነው። የትምህርት ቤት ኢንስፔክሽን አገልግሎት ትምህርት ቤቶችን በመማር፣ በማስተማር፣ በትምህርት አመራር፣ በተማሪዎች የትምህርት አፈፃፀም፣ እና በጤና እና ደህንነት መስፈርቶች ላይ የተወሰኑ መመዘኛዎች እየተሟሉ እና እየተጠበቁ መሆናቸውን በማረጋገጥ ይገመግማል። ይህ ደግሞ ተጨማሪ ድጋፍ የሚፈልጉ ትምህርት ቤቶችን በመለየት ድጋፍ የሚያገኙባቸውን ስልቶችን በመጠቆም የማሻሻያ መንገዶችን ይጠቁማል።
ትምህርት ሚኒስቴር የአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ ከተሰጡት ተግባርና ኃላፊነት አንዱ ወጥ በሆነ ሀገራዊ ስታንዳርድ መሰረት የትምህርት አገልግሎት ጥራት በመለካት ለመንግስትና ለሚመለከታቸው አካላት መረጃ መስጠት ነው። በሀገራችን ትምህርት ቤቶች የኢንስፔክሽን አገልግሎት ካገኙ በኋላ እንደ አፈጻጸም ብቃታቸው በአራት ደረጃ ይመደባሉ። ይኸውም በሶስቱም መለኪያዎች (በግብዓት፣ ሂደትና ውጤት) ተገምግመው ያገኙት አማካይ ውጤት ከ50% በታች ከሆነ ደረጃ አንድ፣ ከ50%-69.99% ደረጃ ሁለት፣ ከ70%-89.99% ደረጃ ሶስት ፣ ከ90%-100% ደረጃ አራት ላይ ይመደባሉ። ደረጃ አንድ ላይ የሚያርፉ ትምህርት ቤቶች አፈጻጸማቸው በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ ይህን ውጤት ለማሻሻል ብዙ መስራት የሚጠበቅባቸው ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደረጃ አራት ላይ የሚያርፉ ትምህርት ቤቶች የላቀ አፈጻጸም ያላቸው በመሆኑ ለሌሎች ትምህርት ቤቶች ሞዴል ሆነው ሊያገለግሉ ይችላሉ ተብሎ ይታመናል።

ይህ የትንተና ሰነድ ሀገር አቀፍ የመጀመሪያ ዙር (ከ2012-2014ዓ.ም) የኡ-ክፍል ትምህርት የኢንስፔክሽን አፈፃፀም ውጤት የያዘ ነው። የኢንስፔክሽን አገልግሎት የተሰጣቸው ኡ-ክፍል የአንድ ዓመት የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም የሚያስተምሩና በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ስር የሚገኙ ናቸው። በትንተና ሂደት መረጃ ለመሰብሰብና ለመተንተን የሚገኙባቸውን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ኮድ መሠረት በማድረግ የተሰበሰበ ሲሆን የኢንስፔክሽን አገልግሎት በተሰጠባቸው ሶስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ አንዳንዶቹም የሚሰጡትን የትምህርት ፕሮግራም ከአንድ ዓመት ወደ ሁለት ዓመት እያሳደጉ ይገኛል።

የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ጥራት መጠበቅ ጉልህ ድርሻ ያለው በመሆኑ የትምህርት አመራሮች፣ መምህራንና ባለድርሻ አካላት ለቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ጥራት መሻሻልና የኢንስፔክሽን አፈፃፀም ደረጃ ለማሳደግ ያለውን ፋይዳ በመገንዘብ ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ትኩረት አድርገው መስራት ይጠበቅባቸዋል።

2. ዓላማ

ይህ የትንተና ሰነድ ዋና እና ዝርዝር ዓላማዎችን ይዟል: -

2.1 ዋና ዓላማ

የዚህ ሰነድ ዋና ዓላማ የኦ-ክፍል ትምህርት የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት አፈፃፀም በመገምገም ለፖሊሲ አውጪዎች፣ ለፈፃሚዎች እና ባለድርሻ አካላት የመፍትሔ ሀሳብ ማቅረብ ነው

2.2 ዝርዝር ዓላማ

- የኦ-ክፍል ትምህርት አሰጣጥ ያለበትን ደረጃ ለማሳወቅ፣
- የኦ-ክፍል ትምህርት በግብዓት፣ ሂደትና ውጤት ስታንዳርዶች ዙሪያ መረጃ ለመስጠት፣
- ውጤታማ የሆነ የኦ-ክፍል ትምህርት መርሐ-ግብር ግብዓት ለመስጠት፣
- የኦ-ክፍል ትምህርት ተግዳሮት የሆኑ ጉዳዮችን ለይቶ ለማመላከት፣
- ለኦ-ክፍል ትምህርት ጥራት ለማሻሻል የሚረዱ ሐሳቦችንና ስልቶችን ለመጠቆም፣

2.3 አስፈላጊነት

ሕፃናት ከዕድሜአቸው ለጋነት የተነሳ በማንኛውም ጊዜ ከየትኛውም የሕብረተሰብ ክፍል የበለጠ ለአደጋና ጉዳት የተጋለጡ በመሆናቸው ልዩ ጥበቃ፣ አያያዝና እንክብካቤ እንደሚያስፈልጋቸው ግልፅ ነው። በተጨማሪም የአካል ጉዳት ያለባቸው ህፃናት ጉዳታቸው እያደገ ሲመጣ የከፋ እንዳይሆን ቅድመ ዕርዳታ (Early support) እንዲያገኙና የወደፊት ህይወታቸው ውጤታማ እንዲሆን የምናዘጋጅበት የትምህርት ዕርከን መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። የቅድመ - አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሕፃናት የወደፊት ህይወታቸው መሠረት የሚጣልበትና ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ዝግጁ የሚደረጉበት ነው። በሀገራችን የሚሰጠው የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት የተለያዩ አተገባበሮች ሲኖሩት አብዛኛዎቹ ሕፃናት የአንድ ዓመት የትምህርት ፕሮግራም በሚሰጥበት "የኦ-ክፍል" ሲሆን ትምህርቱ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ በተደራቢነት እየተሰጠ ይገኛል።

የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም በወደፊቱ የሀገር ኢኮኖሚ ዕድገት ላይ የሚኖረው ኢኮኖሚያዊ አስተዋጽኦ የላቀ ከመሆኑም ባሻገር በህፃናት አካላዊም ሆነ አእምሯዊ ዕድገት ላይ ጠንካራ መሠረት የሚጣልበት እና ማህበራዊ እኩልነትን የሚያጠናክር በመሆኑ አስፈላጊነቱ የጎላ ነው።

3. የኦ-ክፍል ደረጃ ምደባ

ኦ-ክፍሎቹ የሚገመገሙባቸው ስታንዳርዶች እንደ አስፈላጊነታቸው የተለያየ ክብደት የተሰጣቸው ሲሆን ከመለኪያዎች ጋር ያላቸው ትስስርም ከታች በቀረበው ሠንጠረዥ ላይ ተቀምጧል።

ሠንጠረዥ፡ 1የመለኪያዎችና የስታንዳርዶች ትስስር

መለኪያዎች	ስታንዳርዶች	የተሰጠ ክብደት
ግብዓት	6	25%
ሂደት	12	45%
ውጤት	4	30%
ድምር	22	100%

ሠንጠረዥ 1፡ እንደሚያመለክተው ለስድስት የግብዓት ስታንዳርዶች 25 በመቶ፣ ለአሥራ ሁለት የሂደት ስታንዳርዶች 45 በመቶ እና ለአራት የውጤት ስታንዳርዶች 30 በመቶ ክብደት ተሰጥቷቸዋል። ከሕፃናቱ አካላዊ ፣ አዕምሯዊና ማህበራዊ ዕድገቶች ጋር የሚገናኙ ውጤቶች ለአራት የኦ-ክፍል ትምህርት ኢንስፔክሽን የውጤት ስታንዳርዶች ክብደት ተሰጥቷቸዋል።

በዚህ የመጀመሪያ ዙር የኢንስፔክሽን አገልግሎትም ከላይ የተጠቀሱትን የግብዓት፣ የሂደትና የውጤት መለኪያዎችን መሠረት በማድረግ በመለኪያዎቹ ሥር በተቀመጡት ስታንዳርዶች እያንዳንዱን የኦ-ክፍል ትምህርት በመገምገም ያለበትን ደረጃ ለመለየት ጥረት ተደርጓል። ከተገኘው የኢንስፔክሽን ምዘና በመነሳትም የመጀመሪያ ዙር የኢንስፔክሽን አፈጻጸም ትንተና ተዘጋጅቷል። ይህ የመጀመሪያ ዙር የኢንስፔክሽን አፈጻጸም ትንተና ለትምህርት ቤቶች የሚሰጠው የኢንስፔክሽን አገልግሎት የኦ-ክፍል የትምህርት ጥራት ለማረጋገጥ ያለው አስተዋጽኦ ላይ ያተኮረ ነው።

4. የመረጃ አሰባሰብና ትንተና ሂደት

4.1 የመረጃ አሰባሰብ

በትምህርትና ስልጠና ዘርፍ በማስረጃ ላይ የተመሰረተ የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓት እንዲመጣ የመረጃ ትንተና ውሳኔዎችን የበለጠ ሳይንሳዊ በማድረግ እና በትምህርት ጥራት ማሻሻል ዙሪያ በቂ ግንዛቤ ተጨብጦበት ይበልጥ ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲሰሩ ለመርዳት ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። ከክልል መረጃዎችን ወጥነት ባለው የመረጃ መሰብሰቢያ ቅፅ እንዲሰበሰብ በማድረግ ፣ የተሰበሰቡ መረጃዎችን የማደራጀት፣ የመፈተሽ፣ የማጽዳት፣ የመቀየር ፣ የመቅረጽ፣ የመተንተንና ምቹ የማድረግ ስራዎች ተከናውኗል።

በዚህ መሰረት የኦ-ክፍል ትምህርት ኢንስፔክሽን አፈፃፀም ትንተና የተዘጋጀበት ሂደት፡

- ከእያንዳንዱ ወረዳ በክልሎች አማካኝነት በአገር አቀፍ ደረጃ በተዘጋጁት የኦ-ክፍሎች ኢንስፔክሽን ማዕቀፍ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ/ቼክ-ሊስት በመጠቀም፤
- ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የትምህርት መረጃ አስተዳደርና ሥራ ክፍል በተሰጣቸው የኦ-ክፍሎች ኮድ [1]በማናበብ፤
- የኦ-ክፍል ትምህርት ኢንስፔክሽን ማዕቀፍ 22 ስታንዳርዶችን (የግብዓት፣ ሂደትና ውጤት) መለኪያዎች መሠረት የተሰበሰቡ የእያንዳንዱ የኦ-ክፍል መረጃዎች የማደራጀት ስራዎች ተከናውኗል።

4.2 የትንተና ዘዴዎች

በስታትስቲክስ በሚታወቁት ሁለት ዓይነት የትንተና ዘዴዎች ማለትም ገላጭ (descriptive statistics) እና ዓይነታዊ (inferential statictics) ሲሆኑ በዚህ ትንተና ጥቅም ላይ የዋለው ገላጭ (descriptive statistics) ነው። ለትንተናው ጥቅም ላይ የዋለው የኮምፒውተር ሶፍትዌር ማይክሮሶፍት ኤክስኤልና ፖወር ቢ.. አይ ዴስክቶፕ (*Ms excel and Power BI desktop*) በመጠቀም ***ሰንጠረዦችን ግራፎችን*** በመውሰድ ትንተናው ተሰርቷል። የትንተናው ትኩረት ነጥቦች በዋናነት የትምህርት ፍትሐዊነት፣ ጥራት፣ የሠው ሀይል ልማት፣ በትክክል እነዚህን አራቱን ወይንስ ፍትሃዊነት፣ ጥራት፣ ወይንም ምቹ የትምህርት ቤት አካባቢ፣ በቂ የመምህርና የሰው ሃይል፣ የመማር ማስተማር ዘዴ ፣ የሕጻናት የመማር ውጤት... ወዘት የመሳሰሉትን አቢይ የትኩረት መስኮች ሲሆኑ ለንፅፅርም በክልሎች መካከል፣ በገጠርና በከተማ የሚገኙ ኦ-ክፍሎች በትምህርት ቤት መሻሻል የትኩረት መስኮች ዙሪያ የባለድርሻ አካላትን ከፍተኛ ድጋፍና ክትትል የሚፈልጉ የኢንስፔክሽን አፈፃም ደረጃዎችን ዳስሶ የተሰራ ነው።

[1] የቅድመ መደበኛ ትምህርት ኦ -ክፍሎች የራሳቸው መለያ ኮድ ስለሌላቸው በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ስር የሚገኙ ስለሚገኙ የትምህርት ቤቱን ኮድ ለመለያ ጥቅም ላይ ውሏል።

5. የመጀመሪያው ዙር የኦ-ክፍል ኢንስፔክሽን

በመጀመሪያው ዙር (ከ2012-2014 ዓ.ም) የተከናወነው የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት መስጫ *"የኦ-ክፍል"* ኢንስፔክሽን እንደሚያመለክተው ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት በደረጃ አንድ ላይ ያረፉ ናቸው። ደረጃ አራት ላይ ያረፉ የሉም። በዚህ ትንተና በ2012 በጀት ዓመት ከትግራይ ክልል የተሰበሰበ የ200 ኦ-ክፍል ኢንስፔክሽን መረጃዎች በዚህ ትንተና ጥቅም ላይ የዋሉ ሲሆን በወቅቱ የተሰበሰበው መረጃ ከመተው ይልቅ በዚህ ሀገር አቀፍ ሪፖርት ማካተቱ ገንቢ በመሆኑ ተካትቷል።

ሠንጠረዥ፡ 2ከ2012-2014 ዓ.ም የተከናወነ የኦ-ክፍል ኢንስፔክሽን አፈፃፀም በደረጃ

ክልል(ከተማ አስተዳደር)	ዕቅድ	ክንውን	ክንውን(%)	ደረጃ-1		ደረጃ-2		ደረጃ-3		ደረጃ-4	
				ቁጥር	መቶኛ	ቁጥር	መቶኛ	ቁጥር	መቶኛ	ቁጥር	መቶኛ
ሐረሪ	4	47	87.0%	7	14.9%	34	72.3%	6	12.8%	-	-
ሲዳማ[2]	1,043	882	84.6%	267	30.3%	571	64.7%	44	5.0%	-	-
ሶማሌ	515	432	83.9%	379	87.7%	51	11.8%	2	0.5%	-	-
ቤኒሻንጉል	479	126	26.3%	83	65.9%	42	33.3%	1	0.8%	-	-
ትግራይ[3]	1,701	200	11.8%	197	98.5%	3	1.5%	-	0.0%	-	-
አማራ	8,677	3,418	39.4%	2,379	69.6%	1,006	29.4%	33	1.0%	-	-
አዲስ አበባ	70	79	112.9%	16	20.3%	60	75.9%	3	3.8%	-	-
አፋር	331	367	110.9%	334	91.0%	32	8.7%	1	0.3%	-	-
ኦሮሚያ	11,741	7,951	67.7%	5,298	66.6%	2,584	32.5%	69	0.9%	-	-
ደቡብ	3,933	2,370	60.3%	1,276	53.8%	1,056	44.6%	38	1.6%	-	-
ደቡብ_ምዕራብ[4]	1,338	367	27.4%	234	63.8%	118	32.2%	15	4.1%	-	-
ድሬዳዋ	76	72	94.7%	33	45.8%	37	51.4%	2	2.8%	-	-
ጋምቤላ	194	66	34.0%	35	53.0%	29	43.9%	2	3.0%	-	-
ሀገር አቀፍ	**30,152**	**16,377**	**54.3%**	**10,538**	**64.3%**	**5,623**	**34.3%**	**216**	**1.3%**		

[2] *የሲዳማ ክልል በ2013 ወደ ክልልነት ከማደጉ በፊት ከደቡብ ክልል በነበረበት ወቅት የተሰበሰበ መረጃ ነው።*

[3] *ትግራይ ክልል በ2012 የትምህርት ዘመን ብቻ የተሰበሰበ የኢንስፔክሽን መረጃዎች ሲሆኑ ከሚቀመጥ ይልቅ በዚህ ሪፖርት ጥቅም ላይ ውሏል።*

[4] *አሁን ያለው የሲዳማ ክልል በ2013 ወደ ክልልነት ከማደጉ በፊት በደቡብ ክልል በነበረበት ወቅት የተሰበሰበ መረጃ ነው።*


ከ2012-2014ዓ.ም በጀት ዓመት የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም ለሆነው የኦ-ክፍል የኢንስፔክሽን አገልግሎት ተሰጥቷል።

አገልግሎቱ ከተሰጣቸው ውስጥ የተመዘገበው አፈፃፀም ስንመለከት 10,538 (64.3%) ደረጃ አንድ ላይ ወድቀዋል። ደረጃ ሁለት ላይ የሚገኙት ደግሞ 5,623 (34.3%) ብቻ ናቸው። ስታንዳርዱን ያሟሉት 216 (1.3%) ብቻ ናቸው።

ይህ የሚያሳየው መንግስት እና ህብረተሰቡ ለቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት አገልግሎት የተሰጠው ትኩረት አነስተኛ መሆኑን ሲሆን የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ የሚጠይቅ ተግባር ይሆናል። ጉዳዩ የፍትሐዊነት ጥያቄ ውስጥ የሚያስገቡ ጉዳዮችንም የያዘ በመሆኑ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት መስጫ አካበቢዎችን ምቹ በማድረግና በቂ የሰለጠኑ መምህራንን አቅርቦት የሚጠይቅ ተግባር ነው።


5.1 የኦ-ክፍል ትምህርት ኢንስፔክሽን አገልግሎት ስርጭት

የኢንስፔክሽን አገልግሎት የተሰጣቸው የኦ-ክፍል ትምህርት ማሰጫ ስርጭት



5.2 የክልሎች ኦ-ክፍል ኢንስፔክሽን አፈፃፀም በደረጃ

ግራፍ 1 የኦ-ክፍሎች ኢንስፔክሽን አፈፃፀም ደረጃ በክልል



ከላይ በግራፍ 1 እንደተመለከተው በትንተናው ጥቅም ላይ ከዋሉት የክልሎች መረጃዎች የትግራይ ክልል በ2012 የትምህርት ዘመን (ከኮሮና ወረርሽኝ በፊት) የተሰበሰበ ሲሆን ከዚያ በኋላ የክልሉን አጠቃላይ ሁኔታ የሚገልፅ መረጃ አይደለም። ከተሰበሰበው አጠቃላይ መረጃ በተመለከተ የኦ-ክፍል ትምህርት 63.8% ደረጃ አንድ፣ 32.2% ደረጃ ሁለት እና 1.6% ደረጃ ሶስት እንደሆኑ ከተሰበሰበው መረጃ ማረጋገጥ ተችሏል።
ይህ አሀዝ በክልል ደረጃ በአብዛኛዎቹ ተመሳሳይ አፈፃፀም ያላቸው ሲሆን ለቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት መስጫ ኦ-ክፍል ተገቢውን ትኩረት መስጠት እንደሚገባ የሚጠቁም ጉዳይ ነው።

5.3 የክልሎች ኦ-ክፍል ኢንስፔክሽን አፈፃፀም በደረጃ በከተማና በገጠር

በዚህ ትንተና በገጠርና በከተማ ያለውን የኦ-ክፍል ትምህርት ከትምህርት ፍትሐዊነት አንጻር በኢንስፔክሽን አፈፃፀም በደረጃ የተመደቡትን የተዳሰሱበት ነው። በአጠቃላይ ከተሰበሰበው 16,377 የኦ-ክፍል ኢንስፔክሽን መረጃ 1,977 (12.1%) የሚሆኑት በከተማ የሚገኙ ሲሆን 14,400 (87.9%) የሚሆኑት በገጠር የሚገኙ ናቸው።

5.3.1 ኦ-ክፍል ኢንስፔክሽን አፈፃፀም በደረጃ በከተማ

ሠንጠረዥ፡ 3በከተማ የሚገኙ የኦ-ክፍል ኢንስፔክሽን አፈፃፀም ደረጃ በክልል


ክልል(ከተማ አስተዳደር)	ደረጃ-1		ደረጃ-2		ደረጃ-3		ደረጃ-4		ድምር
	ቁጥር	መቶኛ	ቁጥር	መቶኛ	ቁጥር	መቶኛ	ቁጥር	መቶኛ	
ሐረሪ		0%	16	84%	3	16%	-	0%	19
ሲዳማ	2	3%	50	82%	9	15%	-	0%	61
ሶማሌ	1	25%	3	75%		0%	-	0%	4
ቤኒሻንጉል	7	54%	5	38%	1	8%	-	0%	13
አማራ	208	54%	163	43%	12	3%	-	0%	383
አዲስ አበባ	12	18%	53	78%	3	4%	-	0%	68
አፋር	5	71%	2	29%		0%	-	0%	7
ኦሮሚያ	466	43%	582	54%	36	3%	-	0%	1,084
ደቡብ	74	29%	171	67%	11	4%	-	0%	256
ደቡብ_ምዕራብ	28	61%	18	39%		0%	-	0%	46
ድሬዳዋ	10	36%	16	57%	2	7%	-	0%	28
ጋምቤላ	5	62%	3	38%		0%	-	0%	8
ሀገር አቀፍ	818	41%	1,082	55%	77	4%	-	0%	1,977

ሰንጠረዥ 3፡ የኦ-ክፍል አፈጻጸም በደረጃ በከተማ የሚያሳይ ነው። በዚሁ መሠረት በየክልሎቹ በከተማ አስተዳደሮች ውስጥ በሚገኙና የኢንስፔክሽን አገልግሎት ከተሰጣቸው የኦ-ክፍሎች ስንመለከት ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ አማራ፣ አፋር፣ ደቡብ ምዕራብና የጋምቤላ ክልሎች ውስጥ ከሚገኙ ኦ-ክፍሎች መካከል ከ50% በላይ ደረጃ 1 ላይ የተመደቡት ናቸው።

ሐረሪ፣ ሲዳማ፣ ሶማሌ፣ አዲስ አበባ፣ ኦሮሚያ፣ ደቡብና ድሬዳዋ ውስጥ ከሚገኙና የኢንስፔክሽን አገልግሎት ከተሰጣቸው ኦ-ክፍሎች ውስጥ ከ50% በላይ ደረጃ 2 ላይ የተመደቡት ናቸው።

በተለይም ዝቅተኛ ቁጥር የኦ-ክፍል የኢንስፔክሽን አገልግሎት ከተሰጣቸው ክልሎች ውስጥ ሐረሪ፣ ሲዳማና ሶማሌ ክልሎች ከፍተኛ ቁጥር ያለውና ደረጃ 2 ላይ የተመደቡ ኦ-ክፍል ያላቸው ክልሎች ናቸው።

ግራፍ 2 በክልሎች የገጠርና ከተማ ኦ-ክፍል ኢንስፔክሽን አፈፃፀም በደረጃ



በሀገር አቀፍ ደረጃ ከሚገኙትና የኢንስፔክሽን አገልግሎት ከተሰጣቸው ኦ-ክፍሎች ውስጥ 96% የሚሆኑት ከደረጃ በታች መሆናቸውን መረጃው ያሳያል። በዚሁ መሰረት ሶማሌ፣ አፋር፣ ደቡብ ምዕራብና ጋምቤላ ክልሎች ውስጥ የሚገኙና ኢንስፔክሽን የተሰራላቸው የኦ-ክፍል ትምህርት ቤቶች በሙሉ ከደረጃ በታች (ደረጃ 1 ወይም ደረጃ 2) ላይ የተመደቡ ናቸው።

በመሆኑም እነዚህ ኦ-ክፍሎች ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት መሠረት የሚጣልባቸውና የማህበረሰቡን ልዩ ትኩረት የሚፈልጉ እንደመሆናቸው ደረጃቸውን የማሻሻል ስራ ካልተሰራ በተማሪዎቹ ቀጣይ የትምህርት እድገት ላይ ሊያደርስ የሚችለውን አሉታዊ ተጽዕኖ ለመቀነስ ብሎም ለመቅረፍ እንዲቻል በየክልሉ ያሉና የኢንስፔክሽን አገልግሎት ያላገኙ ትምህርት ቤቶች አገልግሎቱን አግኝተው ደረጃቸውን እንዲያውቁ እንዲሁም የኢንስፔክሽን አገልግሎት አግኝተው ከደረጃ በታች የሆኑ የኦ-ክፍል ትምህርት ቤቶች ደረጃ ለማሻሻል ሁሉም ባለድርሻ አካላት የድርሻቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል።

5.3.2 ኦ-ክፍል ኢንስፔክሽን አፈፃፀም በደረጃ በገጠር

ሠንጠረዥ፡ 4በገጠር የሚገኙ የኦ-ክፍል ኢንስፔክሽን አፈፃፀም ደረጃ በክልል

ክልል(ከተማ አስተዳደር)	ደረጃ-1		ደረጃ-2		ደረጃ-3		ደረጃ-4		ድምር
	ቁጥር	መቶኛ	ቁጥር	መቶኛ	ቁጥር	መቶኛ	ቁጥር	መቶኛ	
ሐረሪ	7	25%	18	64%	3	11%	-	0%	28
ሲዳማ	265	32%	521	63%	35	4%	-	0%	821
ሶማሌ	378	88%	48	11%	2	0%	-	0%	428
ቤኒሻንጉል	76	67%	37	33%		0%	-	0%	113
ትግራይ[5]	197	99%	3	2%		0%	-	0%	200
አማራ	2,171	72%	843	28%	21	1%	-	0%	3,035
አዲስ አበባ	4	36%	7	64%		0%	-	0%	11
አፋር	329	91%	30	8%	1	0%	-	0%	360
ኦሮሚያ	4,832	70%	2,002	29%	33	0%	-	0%	6,867
ደቡብ	1,202	57%	885	42%	27	1%	-	0%	2,114
ደቡብ_ምዕራብ	206	64%	100	31%	15	5%	-	0%	321
ድሬዳዋ	23	52%	21	48%		0%	-	0%	44
ጋምቤላ	30	52%	26	45%	2	3%	-	0%	58
ሀገር አቀፍ	9,720	68%	4,541	32%	139	1%	-	0%	14,400

ሰንጠረዥ 4. የኦ-ክፍል አፈጻጸም በደረጃ በገጠር የሚያሳይ ነው። በዚሁ መሠረት በየክልሎቹና በከተማ አስተዳደሮች ውስጥ በሚገኙና የኢንስፔክሽን አገልግሎት ከተሰጣቸው የኦ-ክፍሎች ስንመለከት ትግራይ፣ አፋር፣ ሶማሌ፣ አማራ፣ ኦሮሚያ፣ ደቡብ ምዕራብ ፣ ደቡብ፣ ድሬዳዋና እና ጋምቤላ ክልሎች ውስጥ ከሚገኙ ኦ-ክፍሎች መካከል ከ 50% በላይ ደረጃ 1 ላይ የተመደቡት ናቸው።

ሐረሪ፣ ሲዳማ እና አዲስ አበባ ውስጥ ከሚገኙና የኢንስፔክሽን አገልግሎት ከተሰጣቸው ኦ-ክፍሎች ውስጥ ከ50% በላይ ደረጃ 2 ላይ የተመደቡት ናቸው።


በሀገር አቀፍ ደረጃ በገጠር ካሉት ኦ-ክፍል ኢንስፔክሽን አፈፃፀምን በተመለከተ 9,720 (67.50%) ደረጃ አንድ፣ 4,541 (31.53%) ደረጃ ሁለት እና 139 (0.97%) ደረጃ ሶስት ላይ ይገኛሉ። ሙሉ በሙሉ በሚያስብል ሁኔታ በሁሉም ክልሎች የሚገኙ የገጠር ኦ-ክፍሎች 14,261(99.03%) ደረጃ አንድ እና ደረጃ ሁለት ላይ የሚገኙና በሀገር ዓቀፍ ደረጃ የተቀመጠውን የኦ-ክፍል ትምህርት ስታንዳርድን ማሟላት አልቻሉም ።

[5] የትግራይ መረጃ በ2012 ብቻ የተሰበሰበ በመሆኑ አጠቃላይ የክልሉን የኦ-ክፍሎች ሁኔታን አያሳይም።

በገጠር እና በከተማ የሚገኙ ኦ-ክፍል ኢንስፔክሽን አፈፃፀም በተመለከተ የአፈፃፀም ደረጃቸው በጣም ዝቅተኛ መሆኑ መንግስትና ሌሎች በትምህርት ዘርፉ የተሰማሩ አጋሮች ለቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ጥራት መሻሻል በተለይም የመማሪያ አካባቢዎችን በማሻሻል በኩል በርካታ ቀሪ ስራዎች መኖራቸውን የሚጠቁም መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

5.3.3 ኦ-ክፍል ኢንስፔክሽን አፈፃፀም ሀገር አቀፉ ከከተማ ንፅፅር

ግራፍ 3 የከተማና የገጠር ከሀገር አቀፉ አማካይ አፈፃፀም ንፅፅር በትኩረት መስኮች




በግራፍ 3. የተጠቀሱት የኢንስፔክሽን የትኩረት መስኮች (ግብዓት ሂደትና ውጤት) ባማከለ መልኩ የተቀመጡ ልዩ ልዩ አመላካቾች የገጠር እና የከተማ ት/ቤቶች የአፈፃፀም ውጤቶችን በንፅፅር ያሳያል። በሁለቱ መካከል የሚታየው የትምህርት ቤት ፋሲሊቲ ህንፃዎች፣ የመማርና እንክብካቤ፣ የማስተማር፣ የሥርዓተ ትምህርት አተገባበር፣ የህፃናት ተሳትፎና የውስጥ ብቃት፣ የህፃናት ግለ-ስብዕና፣ የመምህራንና የርዕሰ መምህራን ግለ-ስብእናን የሚያመለክቱ ጉዳዮች በከተማ የሚገኙ ከ5.7% እስከ 6.9% በገጠር ከሚገኙ ኦ-ክፍሎች ጋር ሲነፃፀሩ የተሻለ አፈፃፀም አስመዝግበዋል። በተጨማሪም ከተመላከቱት አመላካቾች መካከል በገጠርም ሆነ በከተማ በሰው ሀይል አደረጃጀት ያለው አፈፃፀም ዝቅተኛ ነው።

በመሆኑም በገጠር እና በከተማ ከሚገኙ የኦ-ክፍሎች መካከል የሚታየውን ሰፊ የአፈፃፀም ልዩነት ለማሻሻል ሁሉም ባለድርሻ አካላት ትኩረት ሰጥተው መስራት ይጠበቅባቸዋል።

5.4 የኦ-ክፍል ኢንስፔክሽን አፈፃፀም በትኩረት መስኮችና በደረጃ

በዚህ ክፍል በትምህርት ቤት መሻሻል ንዑስ የትኩረት መስኮች አንጻር የተተነተነ የኦ-ክፍል ትምህርት የኢንስፔክሽን አፈፃፀም በደረጃ ሲሆን አቢይ ችግሮቻቸውን ለማሳየት በሚያስችል መልኩ የቀረበበት ነው። የትኩረት መስኮቹም የትምህርት ፋሲሊቲ፣ ህንፃዎች፣ የሰው ሀይል፣ የገንዘብ ምንጮች፣ ምቹ የመማሪያ አካባቢ፣ የምድረ ግቢ ገጽታ፣ የሕፃናት እንክብካቤ፣ መማር እና ማስተማር፣ የኦ-ክፍል አስተባባሪ ፣ የኦ-ክፍሉ ማህበረሰብና የህፃናት ግንኙነት፣ የስርዓተ ትምህርት አተገባበር ምዘና፣ የኦ-ክፍል ትምህርት እና የወላጆች/አሳዳጊዎች የማህበረሰብ አጋርነት፣ የህፃናት ተሳትፎ እና የውስጥ ብቃት፣ የህፃናት ግለ-ስብዕና፣ የመምህራንና አስተባባሪ ግለ - ስብዕና፣ የወላጆችና የአካባቢው ማህበረሰብ ተሳትፎ... የተመለከቱ ጉዳዮችን አካትቶ ይዟል። ትንተናው በግብዓት፣ ሂደትና ውጤት መለኪያዎች ተከፋፍሎ ቀርቧል።

5.4.1 የኦ-ክፍል ትምህርት ኢንስፔክሽን አማካኝ አፈፃፀም በክልል




ከላይ ግራፉ የሚያመለክተው የክልሎችና የሀገር አቀፉ የኦ-ክፍል አማካኝ አፈፃፀማቸውንና በኦ-ክፍሎች መካከል ያለውን የውጤት መራራቅን በንፅፅር ያሳያል። በአዲስ አበባ፣ በሐረሪና በደሬዳዋ የሚገኙ ኦ-ክፍሎች በመካከላቸው አነሰተኛ ልዩነትና የተሻለ አማካኝ አፈፃፀም አላቸወ። የሀገር አቀፉን ጨምሮ የሌሎች ክልልች አፈፃፀም ከ50% በታች መሆኑን ያሳያል። ይህም በቅድመ አንደኛ ትምህርት በርካታ ቀሪ ስራዎች እንደሚያስፈልጋቸው መረዳት ተችሏል።

5.4.2 የኦ-ክፍል ኢንስፔክሽን አፈፃፀም በግብዓት የትኩረት መስኮችና በደረጃ

የሚከተለው ግራፍ በግብዓት ንዑስ የትኩረት መስኮች የኦ-ክፍል ትምህርት የኢንስፔክሽ አማካይ አፈፃፀምን በንፅፅር ያሳያል።

ግራፍ 4 የኦ-ክፍሎች ኢንስፔክሽን አፈፃፀም በግብዓት ትኩረት መስኮችና በደረጃ



በግብዓት መለኪያዎች ስር አራት የትኩረት መስኮችን መሰረት በማድረግ የቅድመ አንደኛ ኦ-ክፍልን በኢንስፔክሽን አፈፃፀም በደረጃ ለማነፃፀር ተሞክሯል።


ከግራፉ መረዳት እንደሚቻለው ብቃት ያለው የሰው ሀይል ማሟላትን በተመለከተ ደረጃ ሁለት እና ደረጃ ሶስት ላይ የሚገኙ ኦ-ክፍል አፈፃፀም ከመቁረጫው ነጥብ በታች እንደሆኑ ያሳያል።

ይህ የሚያመለክተው በርካታ ኦ-ክፍል ለደረጃው የሚመጥኑ የሰለጠኑ የኦ-ክፍል ትምህርት መምህራንና ረዳት መምህራን አለማሟላታቸውን ይጠቁማል። በዚህ ምክንያት ደረጃ ሁለት እና ደረጃ ሶስት ላይ የሚገኙ የኦ-ክፍል ትምህርት አፈጻጸም ዝቅተኛ መሆን የኢንስፔክሽን አፈፃፀማቸው ላይ ተፅዕኖ አሳድሯል።

5.4.3 የኦ-ክፍል ኢንስፔክሽን አፈፃፀም በሂደት የትኩረት መስኮችና በደረጃ

የሚከተለው ግራፍ በግብዓት ንዑስ የትኩረት መስኮች የኦ-ክፍል ትምህርት የኢንስፔክሽ አማካይ አፈፃፃምን በንፅፅር ያሳያል።

ግራፍ 5 የኦ-ክፍሎች ኢንስፔክሽን አፈፃፀም በሂደት የትኩረት መስኮችና በደረጃ



በሂደት መለኪያዎች ስር ስድስት የትኩረት መስኮችን መሰረት በማድረግ የቅድመ አንደኛ ኦ-ክፍልን በኢንስፔክሽን አፈፃፀም በደረጃ ለማነፃፀር ተሞክሯል።


ከግራፉ መረዳት እንደሚቻለው ደረጃ ሁለት እና ደረጃ ሶስት ላይ የሚገኙ የኦ-ክፍሎች ብቃት ያለው አስተባባሪዎች አግባብነት ያለው የሰው፣ የገንዘብ እና የንብረት ሃብት አጠቃቀም ስርዓት ዘርግቶ በመተግበር በርካታ ቀሪ ስራዎች መኖራቸውን ማወቅ ተችሏል። በተመሳሳይ የሕፃናትና ኦ-ክፍል ህብረተሰብ አጋርነት፣ የሥርዓተ ትምህርት አተገባበሩና ምዘናውን በተመለከተ ዝቅተኛ አፈፃፀም የተመዘገበበት እንደሆነ ከትንተናው መረዳት ተችሏል።

ይህ የሚያመለክተው በርካታ ኦ-ክፍሎች ወጥነት ያለው የስርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ፣ እንዲሁም ለማስተማሪያ የሚያገለግሉ መጽሀፍትን የማዘጋጀትና የማሟላት ችግሮች መኖራቸውን መገንዘብም ተችሏል። በተመሳሳይ የሰለጠኑ የኦ-ክፍል ትምህርት አስተባባሪዎች አለመሟላታቸው እና የሰው ሀይልና የሀብት አጠቃቀም አፈፃፀም ውጤት ዝቅተኛ ሆኖ ተመዝግቧል።

5.4.4 የኦ-ክፍል ኢንስፔክሽን አፈፃፀም በውጤት የትኩረት መስኮችና በደረጃ

የሚከተለው ግራፍ በውጤት ንዑስ የትኩረት መስኮች የኦ-ክፍል ትምህርት የኢንስፔክሽን አማካይ አፈፃፃምን በንፅፅር ያሳያል።

ግራፍ 6 የኦ-ክፍሎች ኢንስፔክሽን አፈፃፀም በውጤት የትኩረት መስኮችና በደረጃ




በውጤት መለኪያዎች ስር ስድስት የትኩረት መስኮችን መሰረት በማድረግ የቅድመ አንደኛ ኦ-ክፍልን በኢንስፔክሽን አፈፃፀም በደረጃ ለማነፃፀር ተሞክሯል።
ከግራፉ መረዳት እንደሚቻለው ደረጃ ሁለት እና ደረጃ ሶስት ላይ የሚገኙ የኦ-ክፍሎች የህብረተሰብ ተሳትፎና የውስጥ ብቃትን የተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ዝቅተኛ አፈፃፀም መመዝገቡን ከትንተናው መረዳት ተችሏል።

ከትንተናው መረዳት እንደሚቻለው በርካታ ኦ-ክፍሎች የህብረተሰብ ተሳትፎና የኦ-ክፍል ውስጣዊ ብቃት በቂ ትኩረት የሚፈልግ ጉዳይ ነው።

6. ከ2012-2014 ዓ.ም የተከናወነው የኦ-ክፍል ኢንስፔክሽን አፈፃፀም በትኩረት መስኮች

6.1 የትምህርት ፋሲሊቲ፣ ህንፃዎች

ግራፍ 7 የትምህርት ፋሲሊቲ፣ ህንፃዎች




በግራፍ 7 የትምህርት ፋሲሊቲዎችና ህንፃዎች ከማሟላት አንፃር ክልሎች ያለበትን የአፈጻጸም ደረጃ ያሳያል።

ከግራፉ መገንዘብ እንደሚቻለው የሐረሪ ክልል 61% ውጤት በማስመዝገብ በትምህርት ፋሲሊቲዎችና ህንፃዎችን ከማሟላት አንፃር ከሌሎች በተሻለ የአፈጻጸም ደረጃ ላይ የሚገኝ ሲሆን የአፋር ክልል 38% በማከናወን ከሁሉም ክልሎች በአፈጻጸሙ ዝቅ ብሎ ይገኛል። የሀገር አቀፉ አማካይ አፈጻጸም 43% ሲሆን ጋምቤላ በ44%፣ አማራ በ45%፣ ሲዳማ በ49%፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ በ51%፣ ድሬዳዋ በ53%፣ አዲስ አበባ በ57%፣ ሐረሪ በ61% ውጤት ከሀገር አቀፉ አማካይ በላይ ይገኛሉ። በሌላ በኩል ኦሮሚያና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ 42%፣ ሶማሌ 41%፣ አፋር 38% በማከናወን ከሀገር አቀፉ አማካይ ውጤት በታች ያስመዘገቡ ክልሎች ሲሆኑ የደቡብ ክልል ከሀገር አቀፉ አማካይ ጋር (43%) ተመሳሳይ ውጤት አለው። ጋምቤላ፣ አማራና ሲዳማ ክልሎች ከሀገር አቀፉ አማካይ በላይ ቢሆኑም ውጤታቸው ከ50% በታች በመሆኑ ደረጃ1 ላይ የሚገኙ ሲሆን ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ድሬዳዋ፣ አዲስ አበባና ሐረሪ ውጤታቸው 50% እና በላይ በመሆኑ ደረጃ2 ላይ ይገኛሉ። የትምህርት ፋሲሊቲዎችና ህንፃዎችን ከማሟላት አንፃር ከ38%-43% በመፈፀም ከሀገር አቀፉ አማካይ ውጤት በታች ሆነው ደረጃ1 ላይ ያረፉ 6 ክልሎች መኖራቸውን ከግራፉ መረዳት ይቻላል።

6.2 የሰው ኃይል

ግራፍ 8 የሰው ኃይል




በግራፍ 8 በሰው ኃይል አቅርቦት ክልሎች ያለበትን የአፈጻጸም ደረጃ ያሳያል።

ከግራፉ መረዳት እንደሚቻለው የሲዳማ ክልል ለኡ-ክፍሎች የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል ከማቅረብ አንፃር 54% በመፈፀም ከሌሎች በተሻለ የአፈጻጸም ደረጃ ላይ የሚገኝ ሲሆን የአፋር ክልል 34% በማከናወን ከሁሉም ክልሎች በአፈጻጸሙ ዝቅ ብሎ ይገኛል። የሀገር አቀፉ አማካይ አፈጻጸም 40% ሲሆን ደቡብ በ41%፣ አማራ በ44%፣ ጋምቤላ በ48%፣ ሐረሪ በ51%፣ ድሬዳዋ በ52%፣ አዲስ አበባ በ53%፣ ሲዳማ በ54% ውጤት ከሀገር አቀፉ አማካይ በላይ ይገኛሉ። በሌላ በኩል ሶማሌና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ 38%፣ ኦሮሚያ 36%፣ አፋር 34% በማከናወን ከሀገር አቀፉ አማካይ በታች ያስመዘገቡ ክልሎች ሲሆኑ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ከሀገር አቀፉ አማካይ (40%) ጋር ተመሳሳይ ውጤት አለው። ደቡብ፣ አማራና ጋምቤላ ክልሎች ከሀገር አቀፉ አማካይ በላይ ቢሆኑም ውጤታቸው ከ50% በታች በመሆኑ ደረጃ1 ላይ የሚገኙ ሲሆን ሐረሪ፣ ድሬዳዋ፣ አዲስ አበባና ሲዳማ ውጤታቸው 50% እና በላይ በመሆኑ ደረጃ2 ላይ ይገኛሉ። በሰው ኃይል አቅርቦት ከ34%-38% በመፈፀም ከሀገር አቀፉ አማካይ ውጤት በታች ሆነው ደረጃ1 ላይ ያረፉ 3 ክልሎች መኖራቸውን ከግራፉ መገንዘብ ይቻላል።

6.3 የገንዘብ ምንጮች

ግራፍ 9 የገንዘብ ምንጮች




በግራፍ 9 ለኦ-ክፍሎች የሀብት ምንጭ ከማስፋትና ለተቋማቱ የሚያስፈልገውን በጀት ከመመደብ አንፃር ክልሎች ያለበትን የአፈጻጸም ደረጃ ያሳያል።

ከግራፉ መረዳት እንደሚቻለው የሐረሪ ክልል የኦ-ክፍሎችን የሀብት ምንጭ ከማስፋትና ለተቋማቱ የሚያስፈልገውን በቂ በጀት ከመመደብ አንፃር 53% **በመፈፀም ከሌሎች በተሻለ የአፈጻጸም ደረጃ ላይ የሚገኝ ሲሆን የአፋር ክልል** 37% **በማከናወን ከሁሉም ክልሎች በአፈጻጸሙ ዝቅ ብሎ ይገኛል። የሀገር አቀፉ አማካይ አፈጻጸም** 42% **ሲሆን ደቡብ በ**45%**፣ ሲዳማ በ**49%**፣ ድሬዳዋ** 50%**፣ ሐረሪ በ**53% **ውጤት ከሀገር አቀፉ አማካይ በላይ ይገኛሉ። በሌላ በኩል ጋምቤላ** 41%**፣ ሶማሌና አዲስ አበባ** 40%**፣ አማራና ቤኒሻንጉል ጉሙዝ** 39% **እና አፋር** 37% **በማከናወን ከሀገር አቀፉ አማካይ በታች ያስመዘገቡ ክልሎች ሲሆኑ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያና ኦሮሚያ ከሀገር አቀፉ አማካይ** (42%) **ጋር ተመሳሳይ ውጤት አላቸው። ደቡብ እና ሲዳማ ክልሎች ከሀገር አቀፉ አማካይ በላይ ቢሆኑም ውጤታቸው ከ**50% **በታች ስለሆነ ደረጃ**1 **ላይ የሚገኙ ሲሆን ድሬዳዋና ሐረሪ ውጤታቸው** 50% **እና በላይ በመሆኑ ደረጃ**2 **ላይ ይገኛሉ።**

የሀብት ምንጭ ከማስፋትና ለተቋማቱ የሚያስፈልገውን በጀት ከመመደብ አንፃር ከ37%-41% **በመፈፀም ከሀገር አቀፉ አማካይ ውጤት በታች ሆነው ደረጃ**1 **ላይ ያረፉ** 6 **ክልሎች መኖራቸውን ከግራፉ መገንዘብ ይቻላል። በመሆኑም ለኦ-ክፍሎች የሀብት ምንጭ ከማስፋትና የሚያስፈልጋቸውን በጀት በመመደብ በርካታ ሥራዎች በመስራት ለሕፃናቱ ምቹ የመማሪያ አካባቢን መፍጠር ይቻላል።**

6.4 ምቹ የመማሪያ አካባቢና የምድረ ግቢ ገጽታ

ግራፍ 10 ምቹ የመማሪያ አካባቢና የምድረ ግቢ ገጽታ




በግራፍ 10 ምቹ የመማር ማስተማር አካባቢ ከመፍጠር አንፃር ክልሎች ያሉበትን የአፈጻጸም ደረጃ ያሳያል።

ከግራፉ መረዳት እንደሚቻለው የሐረሪ ክልል ምቹ የመማር ማስተማር አካባቢ ከመፍጠር አንፃር 51% በመፈጸም ከሌሎች በተሻለ የአፈጻጸም ደረጃ ላይ የሚገኝ ሲሆን የአፋር ክልል 36% በማከናወን ከሁሉም ክልሎች በአፈጻጸሙ ዝቅ ብሎ ይገኛል። የሀገር አቀፉ አማካይ አፈጻጸም 44% ሲሆን ደቡብ በ45%፣ ጋምቤላና ቤኒሻንጉል ጉሙዝ በ47%፣ ድሬዳዋ በ48%፣ አዲስ አበባና ሲዳማ በ50% እና ሐረሪ በ51% ውጤት ከሀገር አቀፉ አማካይ በላይ ይገኛሉ። በሌላ በኩል አማራ 43%፣ ሶማሌ 42% እና አፋር 36% በማከናወን ከሀገር አቀፉ አማካይ በታች የሆኑ ክልሎች ሲሆኑ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያና ኦሮሚያ ከሀገር አቀፉ አማካይ 44% ጋር ተመሳሳይ ውጤት አላቸው። ደቡብ፣ ጋምቤላ፣ ቤኒሻንጉልና ድሬዳዋ ክልሎች ከሀገር አቀፉ አማካይ በላይ ቢሆኑም ውጤታቸው ከ50% በታች በመሆኑ ደረጃ1 ላይ የሚገኙ ሲሆን አዲስ አበባ፣ ሲዳማና ሐረሪ ውጤታቸው 50% እና በላይ በመሆኑ ደረጃ2 ላይ ይገኛሉ። ምቹ የመማር ማስተማር አካባቢ ከመፍጠር አንፃር ከ36%-43% በመፈፀም ከሀገር አቀፉ አማካይ ውጤት በታች ሆነው ደረጃ1 ላይ ያረፉ 3 ክልሎች መኖራቸውን ከግራፉ መገንዘብ ይቻላል።

6.5 መማር እና እንክብካቤ

ግራፍ 11 መማር እና እንክብካቤ




በግራፍ 11 ከመማርና እንክብካቤ አንፃር ክልሎች ያለበትን የአፈጻጸም ደረጃ ያሳያል።

ከግራፉ መረዳት እንደሚቻለው የሐረሪ ክልል ከመማርና እንክብካቤ አንፃር 66% በመፈፀም ከሌሎች በተሻለ የአፈጻጸም ደረጃ ላይ የሚገኝ ሲሆን የአፋር ክልል 40% በማከናወን ከሁሉም ክልሎች በአፈጻጸሙ ዝቅ ብሎ ይገኛል። የሀገር አቀፉ አማካይ አፈጻጸም 48% ሲሆን ቤኒሻንጉል ጉሙዝና ደቡብ በ50%፣ ጋምቤላ በ52%፣ ድሬዳዋ በ54%፣ ሲዳማ በ56%፣ አዲስ አበባ በ60% እና ሐረሪ በ66% ውጤት ከሀገር አቀፉ አማካይ በላይ ውጤት ያስመዘገቡ ሲሆን ደረጃ2 ላይ አርፈዋል። በሌላ በኩል አማራና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ 47%፣ ሶማሌ 43% እና አፋር 40% ውጤት በማምጣት ከሀገር አቀፉ አማካይ በታች የሆኑ ክልሎች ሲሆኑ አራቱም ደረጃ አንድ ላይ አርፈዋል። ኦሮሚያ ከሀገር አቀፉ አማካይ 48% ጋር ተመሳሳይ ውጤት አለው። ከመማርና እንክብካቤ አንፃር ከ40%-47% በመፈፀም ከሀገር አቀፉ አማካይ ውጤት በታች ሆነው ደረጃ1 ላይ ያረፉ 4 ክልሎች መኖራቸውን ከግራፉ መገንዘብ ይቻላል።

6.6 ማስተማር

ግራፍ 12 ማስተማር




በግራፍ 12 በማስተማር የትኩረት መስክ ስር በሚገኙ 3 ስታንዳርዶች ማለትም መምህራን የሕጻናቱን የእድገት ፍላጎት፣ ፍጥነትና የትምህርት ዕቅድ በማቀድና ለሁሉም ህፃናት ተስማሚና ህፃን ተኮር የማስተማር እና የእንክብካቤ ስነ-ዘዴዎችን መጠቀም ያሳያል። ከነዚህ ስታንደርዶች አንፃር ከሀገር አቀፉ 49% አፈፃፀም አንፃር ሲታይ የሐረሪ 63% እና የአዲስ አበባ 62% የተሻለ አፈፃፀም አስመዝግበዋል።

በሌላ መልኩ የሶማሌና የአፋር ክልሎች በአንፃሩ ዝቅተኛ አፈፃፀም ላይ እንደሚገኙና የተቀሩትም ስምንት ክልሎች በተመሳሳይ ከሀገር አቀፍ ዝቅተኛ አማካኙ ውጤት 49% ጋር ተመሳሳይ እና ተቀራራቢ ውጤት ላይ እንደሆኑና በተለይም የኦሮምያና የአማራ ክልሎች ግን ከፍተኛ ቁጥር የኡ-ክፍል ያላቸው በመሆኑ የሀገር አቀፍ አማካኝ ውጤት አፈፃጸምን ወደ ደረጃ አንድ ላይ እንዲወድቅ አድርጎታል።

6.7 ርዕሰ መምህሩ (አስተባባሪ)

ግራፍ 13 ርዕሰ መምህሩ(አስተባባሪ)



በግራፉ 13 እንደተገለፀው የርዕሰ መምህራን / አስተባባሪ ፣ የኦ-ክፍሉ ማህበረሰብና የህፃናት የትኩረት መስክ ትምህርት ቤቱ አግባብነት ያለው የሰው፣ የገንዘብ እና የንብረት ሃብት አጠቃቀም ስርዓት እና በህፃናት መካከል በመፈቃቀር፣ በመከባበርና በመተሳሰብ ላይ የተመሰረተ ግንኙነት መፈጠሩን ያመለክታል።


ከዚህ አንፃር የሐረሪ ክልል፣ የጋምቤላ፣ ሲዳማ፣ ድሬዳዋ፣ ቤንሻንጉል፣ ከሀገር አቀፉ አማካኝ ውጤት 44% ጋር ሲነፃፀርም የተሻሻለ እንደሆነ መረጃው ያሳያል።

በሌላ መልኩ የኦሮሚያ 42% እና የአፋር (37%) ክልሎች ከሀገራዊ የትኩረት መስክ ረገድ ሲታይ ዝቅ ያለ አፈፃፀም ማስመዝገባቸውን እንረዳለን።

በመሆኑም አንድ የኦ-ክፍል ትምህርት ያሉትን ሁሉንም ሀብቶች አሟጦ በመጠቀም ከተፈላጊውን የብቃት ደረጃ ላይ መድረስ ስለሚያስችለው ለጉዳዩ ከፍተኛ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል።

6.8 የኦ-ክፍሉ ማህበረሰብና የህፃናት ግንኙነት

ግራፍ 14 የትም/ቤቱ ማህበረሰብና የህፃናት ግንኙነት




በግራፍ 14 የተቀመጠው የኦ-ክፍሎች የትንተና ግኝት በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብና በህፃናት መካከል በመፈቃቀርና በመከባበር ላይ የተመሰረተ ግንኙነት መፈጠሩን ይገመግማል። ከዚህ አንፃር ከሀገር አቀፉ አማካይ 45% ረገድ ሲታይ የሐረሪ ክልል 64%፣ አዲስ አበባ 59% ማስመዝገባቸው የሚበረታታ ውጤት ነው። ሌሎች ክልሎችም በተዋረድ ሲዳማ፣ ትግራይ፣ ድሬዳዋ፣ ቤኒሻንጉልና ጋምቤላ ተቀራራቢ አፈፃፀም አላቸው። በሌላ መልኩ ኦሮሚያ፣ አማራና ሶማሌ ክልሎች ከሀገር አቀፉ አማካኝ አፈጻፀም ወርደው 43% ሲገኙ የአፋር ክልል ግን 40% በማስመዝገብ የበለጠ ዝቅ ብሏል።

በመሆኑም ዝቅተኛ አፈፃፀም ያስመዘገቡ ክልሎች ትኩረት ሰጥተው የኦ-ክፍሎችን በማህበረሰብና በህፃናት ግንኙነት ላይ የተመሰረተውን የተሻለ አፈፃፀም ደረጃ ላይ ለማምጣት ሁሉም የበኩሉን ድርሻ ሊወጣ ይገባል።

6.9 የስርዓተ ትምህርት አተገባበርና ምዘና


ግራፍ 15 የስርዓተ ትምህርት አተገባበርና ምዘና



በግራፍ 15 የተቀመጠው ሥርዓተ ትምህርቱ ተገቢነት ያለው፣ አሳታፊ እና የህፃናቱን የእድገት ደረጃ፣ ፍላጎቶችና ልዩነት ላይ የተቀመጠ የትንተና ግኝትን ያመለክታል። በመሆኑም ስርዓተ ትምህርቱ አሳታፊና የተማሪዎችን የዕድገት ደረጃ ስለመከተሉ፣ ት/ቤቱ የተከታታይ ምዘና ስለመተግበሩ፣ መምህራን የተዘጋጀውን ሥርዓተ ትምህርት ጠንቅቀው ስለማወቃቸው በሚሉ ጉዳዮች ሐረሪ፣ አዲስ አበባ፣ ሲዳማ፣ ድሬዳዋና ጋምቤላ ክልሎች ከ50% እስከ 60% ውጤት አስመዝግበዋል። በሌላ መልኩ የተቀሩት ዘጠኝ ክልሎች ከአማካኙ ባነሰ ውጤት ማስመዝገባቸው መረጃዎች ያሳያሉ። በመሆኑም በቀጣይ በየደረጃው የሚገኙ የትምህርት አመራርና ባለሙያዎች የተከታታይ ምዘና ሥርዓትን በማጠናከር ድጋፍ፣ ክትትልና ግምገማ ሥርዓቱ አሳታፊ እና የህፃናቱን የእድገት ደረጃ፣ ፍላጎቶችና ልዩነት ያገናዘበ በማድረግ እንዲሠሩ ይጠበቅባቸዋል።

6.10 የትምህርት ቤት፣ የወላጆች/አሳዳጊዎችና የማህበረሰብ አጋርነት

ግራፍ 16 የትምህርት ቤት፣ የወላጆች/አሳዳጊዎችና የማህበረሰብ አጋርነት




በግራፍ 16 የትምህርት ቤት፣ የወላጆች/አሳዳጊዎችና የማህበረሰብ አጋርነትን ይመለከታል። በዚሁ መሠረት የትምህርት ቤት፣ የወላጆች/አሳዳጊዎችና የማህበረሰብ አጋርነትን በሚመለከት በአፋር፣ አማራ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ሶማሌ ክልሎች ውስጥ የሚገኙና የኢንስፔክሽን አገልግሎት የተሰጣቸው ኦ-ክፍሎች አፈፃፀማቸው ከሀገር አቀፍ አማካኙ በታች ሲሆን በሌሎቹ የቀሩት ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የሚገኙ የኦ-ክፍል ትምህርት ቤቶች አፈጻጸም ከሀገር አቀፍ አማካኝ ውጤት (45%) በላይ ነው።

በመሆኑም በቀጣይ በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የወላጆች/አሳዳጊዎችና የማህበረሰብ አጋርነትን በማጎልበትና እነዚህ ትምህርት ቤቶች ለቀጣይ የትምህርት እርከን መሰረት የሚጣልበት የአካባቢውን ማህበረሰብ ልዩ ትኩረት የሚፈልግ ጉዳይ ነው። የኦ-ክፍል ትምህርት ደረጃ ለማሻሻል ወላጆች ግብዓቶችን፣ ገንዘብ፣ ቁሳቁስ ... ወዘተ በማሟላት፣ የዕውቀት እና የጉልበት ድጋፍ ማድረግ እንዲሁም የብቃት ደረጃቸውን ለማሻሻል የወላጆች/አሳዳጊዎች ኮሚቴ ውስጥ ተሳትፎ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

6.11 የህፃናት ተሳትፎ እና የውስጥ ብቃት

ግራፍ 17 የህፃናት ተሳትፎ እና የውስጥ ብቃት




በግራፍ 17 የሕጻናት ተሳትፎ እና የውስጥ ብቃት ይመለከታል። በዚሁ መሠረት የኦ-ክፍል ትምህርት ቤቶች በሀገር አቀፍ ደረጃ የተቀመጡ የትምህርት ተሳትፎና የውስጥ ብቃት /Internal Efficiency/ የትምህርት ልማት ዘርፍ መርሃ-ግብር ግቦችን ማሳካትን በሚመለከት በትግራይ፣ አፋር እና ሶማሌ ክልሎች ውስጥ የሚገኙና የኢንስፔክሽን አገልግሎት የተሰጣቸው ኦ-ክፍሎች አፈፃፀማቸው ከሀገር አቀፍ አማካኙ በታች ሲሆን በሌሎቹ የቀሩት ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች (ጋምቤላ፣ ደቡብ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ድሬዳዋ፣ ሲዳማ አዲስ አበባ እና ሐረሪ) ውስጥ የሚገኙ የኦ-ክፍል ትምህርት ቤቶች አፈጻጸም ከሀገር አቀፍ አማካኝ ውጤት (45%) በላይ ነው።

በተለይም ብዙ የኦ-ክፍል ያላቸው የአማራና ኦሮሚያ ክልሎች ከሀገር አቀፍ አማካኝ ውጤት ጋር ተመሳሳይ ውጤት አላቸው። በመሆኑም በቀጣይ በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የሕጻናት ተሳትፎ እንዲሻሻል፣ የትምህርት ቤቶቹ ውስጣዊ ብቃት እንዲጎለብት እና ትምህርት ቤቶች ለቀጣይ የትምህርት እርከን መሰረት የሚጣልባቸው በመሆኑ በትምህርት ቤቶቹ በቅርበት የሚገኙ የመንግስት አስተዳደር አካላትና የአካባቢውን ማህበረሰብ ልዩ ትኩረት የሚያስፈልገው ስለሆነ የኦ-ክፍሎች ደረጃ ለማሻሻል ሁሉም ባለድርሻ አካላት ጠንክረው መሥራት ይጠበቅባቸዋል።

6.12 የህፃናት ግለ-ስብዕና

ግራፍ 18 የህፃናት ግለ-ስብዕና




በግራፍ 18 የህፃናት ግለ-ስብዕናን ይመለከታል። በዚሁ መሠረት የኡ-ክፍል ትምህርት ቤቶች ህፃናት በመልካም ስነ-ምግባር የታነጹና አካባቢን የመንከባከብ ዝንባሌ ያላቸው መሆኑ በተግባር የሚረጋገጥበት ስለመሆኑ በሚመለከት በትግራይ ፣ አፋር እና ሶማሌ፣ አማራ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝና ደቡብ ምዕራብ ክልሎች ውስጥ የሚገኙና የኢንስፔክሽን አገልግሎት የተሰጣቸው ኡ-ክፍሎች አፈፃፀማቸው ከሀገር አቀፍ አማካኝ ውጤት (55%) በታች ሲሆን በሌሎቹ የተቀሩት ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች (ጋምቤላ፣ ደቡብ፣ ድሬዳዋ፣ ኦሮሚያ፣ ሲዳማ አዲስ አበባ እና ሐረሪ) ክልሎች ውስጥ የሚገኙ የኡ-ክፍል ትምህርት ቤቶች አፈጻጸም ከሀገር አቀፍ አማካኝ ውጤት (55%) በላይ ነው።

በተለይም ህጻናቱን በመልካም ስነ-ምግባር ታንጸው እንዲያድጉ ለማድረግ የመጀመሪያው ትምህርት እርከን ይህ የኡ-ክፍል ነው። በመሆኑም በቀጣይ በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የሕጻናት ግለ-ስብዕና እንዲሻሻል እንዲሁም የህጻናቱ ማህበራዊ ግንኙነት እንዲጎለብትና ትምህርት ቤቶቹ ለቀጣይ የትምህርት እርከን መሰረት የሚጣልባቸው በመሆኑ በትምህርት ቤቶቹ በቅርበት የሚገኙ የመንግስት አስተዳደር አካላት እና የአካባቢውን ማህበረሰብ ልዩ ትኩረት የሚፈልግና በመሆኑ የትምህርት ቤቶችን ደረጃ ለማሻሻል ሁሉም ባለድርሻ አካላት ጠንክረው መሥራት ይጠበቅባቸዋል።

6.13 የመምህራንና የርዕሰ መምህር/አስተባባሪ ግለ - ስብዕና


ግራፍ 19 የመምህራንና የርዕሰ መምህር/አስተባባሪ ግለ - ስብዕና



በግራፍ 19 የኦ-ክፍሉ አስተባባሪዎች ግለ-ስብዕና በተመለከተ ከሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የሚጠበቀውን ግለ-ስብዕና በመላበስ ረገድ አብዛኛዎቹ ክልሎች በሀገር አቀፍ ደረጃ ከተመዘገበው ውጤት ተመሳሳይና በላይ የሚገኙ ሲሆን በተለይ ሐረሪ 67 % ፣ አዲስ አበባ 66 % እና ሲዳማ 61% ክልል የኦ ክፍል መምህራን፣ ርዕሰ መምህራን /አስተባባሪዎች መካከል ጥሩ ተግባቦት እና መስተጋብር ያላቸው እንዲሁም በተሻለ ደረጃ ሕጻናትን የሚያከብሩና በተጠያቂነት ስሜት የሚሰሩ ሲሆን በተለይ ሶማሌ 45% እና በአፋር 41% ክልሎች የሚጠበቀውን ግለ-ስብዕና ከመላበስ አንፃር በሀገር ዓቀፍ ደረጃ ከተመዘገበው አማካይ ውጤት በታች ናቸው ።

6.14 የወላጆችና የአካባቢው ማህበረሰብ ተሳትፎ

ግራፍ 20 የወላጆችና የአካባቢው ማህበረሰብ ተሳትፎ



በግራፍ 21 የወላጆችና የአካባቢው ማህበረሰብ ተሳትፎ በተመለከተ አብዛኛዎቹ ክልሎች የሚጠበቀውን ተሳትፎ ከመወጣት አንፃር ከሚጠበቀው ደረጃ በታች ላይ የሚገኙ ቢሆንም ከወላጆች/ ከአሳዳጊዎች፣ ከአካባቢው ማህበረሰብና ከአጋር ድርጅቶች ጋር ጠንካራ ግንኙነት በመፍጠር ለትምህርት ቤቶቹ ድጋፍ በማስገኘት ረገድ ሐረሪ 56 % ፣ ሲዳማ 55 % እና ጋምቤላ 52% ክልሎች በሀገር አቀፍ ደረጃ ከተመዘገበው አማካይ ውጤት በተሻለ ሁኔታ ያስመዘገቡ ሲሆኑ አዲስ አበባ 44% ፣ ደቡብ ምዕራብ 44% ፣ ሶማሌ 42% ፣ አማራ 41% እና አፋር 37% ክልሎች ለአ-ክፍል ትምህርት ድጋፍ በማስገኘት ረገድ በሀገር ዓቀፍ ደረጃ ከተመዘገበው አማካይ ውጤት በታች ናቸው።

7. ምዕራፍ አንድ እና ምዕራፍ ሁለት

እንደሚታወቀው የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጥ ለፍትሐዊነት (GEQIP-E) ፕሮግራም ከጀመረ አምስተኛ አመቱን ይዟል። የአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን በዚህ የፕሮግራም አተገባበር ጊዚያት የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውን ቆይቷል። ከነዚህም ውስጥ ለቅድመ አንደኛ ኦ-ክፍሎች የሚያገለግል የኢንስፔክሽን ማዕቀፍ ማዘጋጀትና በሰነዶቹ ላይ ለክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ተከታታይ ስልጠናዎችን በመስጠት ከ2012 ዓ.ም የትምህርት ዘመን ጀምሮ አገልግሎቱን ሲሰጥ ቆይቷል። በተለይም የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጥ ለፍትሐዊነት ፕሮግራም በተመረጡ 2,160 የምዕራፍ አንድ ኦ-ክፍሎች እንዲሁም በምዕራፍ ሁለት የተመረጡ 8,660 ውጤትን መሰረት ያደረጉ አመልካቾችን /DLR-1.3/ የታቀዱ በመሆናቸው በተያዘላቸው የጊዜ ሰሌዳ በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በየዓመቱ የኢንስፔክሽን አገልግሎት እየተሰጠ መሻሻላቸውም ክትትል እየተደረገበት ሲሰራ ቆይቷል። የፕሮግራሙ ተግባራት ከበጀት ጋር የተገናኙ በመሆናቸው በመንግስት የተለየ ክትትል ሲደረግበት የነበረ ጉዳይ መሆኑ ይታወቃል።

ስለሆነም የአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን ዴስክ ከክልሎች ጋር የኢንስፔክሽኑን አገልግሎት በመስጠት በየዓመቱ መረጃዎች ሲሰበሰቡ ቆይተዋል። የአፈፃፀም ግምገማው የሚያሳየው ከተመረጡት የምዕራፍ አንድ እና የምዕራፍ ሁለት የቅድመ አንደኛ ኦ-ክፍሎች የመማሪያ አካባቢያቸውን በማሻሻል 70% የሚሆኑት የኢንስፔክሽን አፈፃፀም ደረጃቸውን ደረጃ ሁለት መሆኑን ማረጋገጥን ያካትታል።

ከዚህ ጋር በተገናኘ ከዕቅዱ አንፃር የክልሎች አፈፃፀምን የያዘው ትንተና ቀጥሎ ቀርቧል።

ምዕራፍ አንድ ኦ-ክፍሎች ትምህርት ኢንስፔክሽን

7.1.1 ምዕራፍ አንድ ኦ-ክፍሎች የ2012 ዓ.ም ኢንስፔክሽን በክልል እና በደረጃ

ሠንጠረዥ፡ 5ምዕራፍ አንድ የ2012 ኢንስፔክሽን በክልል እና በደረጃ

ክልል(ከተማ አስተዳደር)	ዕቅድ	ክንውን	ክንውን(%)	ደረጃ-1	ደረጃ-2	ደረጃ-3	ደረጃ-4
አዲስ አበባ	11	10	90.9%	3	7		
አፋር	4	4	100.0%	4			
አማራ	518	518	100.0%	360	156	2	
ቤኒሻንጉል	11	4	36.4%	2	2		
ድሬዳዋ	17	17	100.0%	13	4		
ጋምቤላ	2	2	100.0%	2			
ሐረሪ	17	17	100.0%	10	7		
ኦሮሚያ	757	757	100.0%	596	157	4	
ሲዳማ	220	220	100.0%	115	103	2	
ደቡብ	230	230	100.0%	163	61	6	
ሶማሌ	57	56	98.2%	56			
ትግራይ	316	200	63.3%	179	21		
ሀገርአቀፍ	2,160	2035	94.2%	**1,503**	**518**	**14**	

ከላይ በሰንጠረዥ 5 የተመለከተው የምዕራፍ አንድ ኦ-ክፍሎች ኢንስፔክሽን ዕቅድ፣ የክልሎች አፈፃፀም በደረጃ የያዘ ነው።

በ2012 የትምህርት ዘመን በምዕራፍ አንድ የተመረጡት የቅድመ አንደኛ ኦ-ክፍሎች የኢንስፔክሽን አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ሲሰራበት የነበረ ሲሆን በወቅቱ በዓለም ላይ ተከስቶ በነበረው የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት ትምህርት ቤቶች እስከተዘጉበት ጊዜ ድረስ አገልግሎቱ ሲሰጥ ቆይቷል። በሀገር አቀፍ ደረጃ አፈፃፀም ውጤት በተመለከተ 2,035 (94.2%) ለሚሆኑት የኢንስፔክሽን አገልግሎት አግኝተዋል። ከነዚህም ውስጥ 1,503 የሚሆኑት ደረጃ አንድ፣ 518 የሆኑት ደግሞ ደረጃ ሁለት እና 14 ደረጃ ሶስት ሆነዋል።

የአፈፃም ደረጃቸው ደረጃ አንድ ላይ ለሆኑት በ2013 የትምህርት ዘመን የኢንስፔክሽን አፈፃፀም ደረጃቸውን ማሻሻል አለማሻሻላቸውን ለማረጋገጥ አገልግሎቱ ተሰጥቷቸዋል።

7.1.2 ምዕራፍ አንድ ኦ-ክፍሎች የ2013 ኢንስፔክሽን በክልል አፈፃፀም በደረጃ

ከታች በሰንጠረዥ የተመለከተው የምዕራፍ አንድ ኦ-ክፍሎች ኢንስፔክሽን ዕቅድ፣ የክልሎች አፈፃፀም በደረጃ የያዘ ነው።

ሠንጠረዥ፡ 6የምዕራፍ አንድ ኦ-ክፍሎች ኢንስፔክሽን ዕቅድ፣ የክልሎች አፈፃፀም በደረጃ

ክልል/ከተማ አስተዳደር	ዕቅድ	ከንውን	ከንውን(%)	ደረጃ-1	ደረጃ-1 (%)	ደረጃ-2	ደረጃ-2 (%)	ደረጃ-3	ደረጃ-3 (%)	ደረጃ-4	ደረጃ-4 (%)
አዲስ አበባ	3	3	100%	1	33%	2	67%				-
አፋር	4	4	100%	2	50%	2	50%		0%		0%
አማራ	360	264	73%	184	70%	80	30%		0%		0%
ቤኒሻንጉል	2	1	50%		0%	1	100%		0%		0%
ድሬዳዋ	13	13	100%	2	15%	10	77%	1	8%		0%
ጋምቤላ	2	2	100%	2	100%		0%		0%		0%
ሐረሪ	10	10	100%	7	70%	3	30%		0%		0%
ኦሮሚያ	596	531	89%	306	58%	225	42%		0%		0%
ሲዳማ	115	84	73%	35	42%	49	58%		0%		0%
ደቡብ	163	56	34%	22	39%	34	61%		0%		0%
ሶማሌ	56	56	100%	53	95%	3	5%		0%		0%
ሀገርአቀፍ	1,324	1,024	68%	614	60%	409	40%	1	1%		0%

ከላይ በሰንጠረዥ የተመለከተው የምዕራፍ አንድ ኦ-ክፍሎች ኢንስፔክሽን ዕቅድ፣ የክልሎች አፈፃፀም በደረጃ የያዘ ነው።

በ2013 የትምህርት ዘመን በመጀመሪያው ዙር ኢንስፔክት ተደርገው ደረጃ አንድ ላይ ከነበሩት የምዕራፍ አንድ ኦ-ክፍሎች ውስጥ 1024 (88%) ለሚሆኑት አገልግሎቱ ተሰጥቷቸዋል። አፈፃፀሙ የቀነሰበት ምክንያት ሰሜን የሀገራችን አካባቢዎች ባሉት ቦታ አፋር፣ አማራና የተለያዩ አከባቢዎች የነበሩት አለመረጋጋት ምክንያት በበረው ግጭት ምክንያት ነው። የአፈፃፀም ደረጃቸው በተመለከተ 614(60%) ደረጃ አንድ፣ 409(40%) ደረጃ ሁለት እና 1(1%) ደረጃ ሶስት ላይ ተመድበዋል። ይህም በ2013 የትምህርት ዘመን በድምሩ 410 የኦ-ክፍሎች ከደረጃ አንድ ወደ ደረጃ ሁለት አድገዋል ማለት ነው። በምዕራፍ አንድ ከተመረጡት የኦ-ክፍሎች ውስጥ በ2012 የትምህርት ዘመን 518 እና በ2013 የትምህርት ዘመን 410 በድምሩ 928 (50.3%) በመሆን ደረጃ ሁለት ላይ ተመድበዋል።

ይህም አፈፃፀም ከምዕራፍ አንድ 2,160 ኦ-ክፍሎች ውስጥ የትግራይ ክልል 316 ኦ-ክፍሎችን በመቀነስ በሀገር አቀፍ ደረጃ 1,844 ኦ-ክፍሎችን በዕቅድ ተይዞ እስከ 2014 የትምህርት ዘመን የኢንስፔክሽን አገልግሎት በየዓመቱ ሲሰጥ ቆይቷል።

7.1.3 ምዕራፍ አንድ ኦ-ክፍሎች የ2014 ዓ.ም ኢንስፔክሽን በክልል እና በደረጃ

ሠንጠረዥ፡ 7 ምዕራፍ አንድ ኦ ክፍሎች የ2014 ኢንስፔክሽን በክልል እና በደረጃ

ክልል(ከተማ አሰተዳደር)	ዕቅድ	ደረጃ-1	ደረጃ-2	ደረጃ-3
አፋር	2		2	
አማራ	280		82	
ቤኒሻንጉል	8		2	
ድሬዳዋ	3		2	
ጋምቤላ	2			
ሐረሪ	7		13	3
ኦሮሚያ	371		268	3
ሲዳማ	66		57	
ደቡብ	129		70	2
ሶማሌ	54		9	
ሀገርአቀፍ	922		505	8

በ2014 የትምህርት ዘመን በ2012 ዓ.ም እና በ2013 ዓ.ም ኢንስፔክት ተደርገው ደረጃ አንድ ላይ ከነበሩት የምዕራፍ አንድ ኦ-ክፍሎች ውስጥ 922 (100%) ለሚሆኑት አገልግሎቱ ለመስጠት ታቅዶ ለ513 ተሰጥቷቸዋል። የአፈፃፀም ደረጃቸው በተመለከተ 505 ደረጃ ሁለት እና 8 ደረጃ ሶስት ላይ ተመድበዋል። ይህም በ2014 የትምህርት ዘመን በድምሩ 513 የኦ-ክፍሎች ከደረጃ አንድ ወደ ደረጃ ሁለት አድገዋል ማለት ነው። በምዕራፍ አንድ ከተመረጡት የኦ-ክፍሎች ውስጥ ከ2012-2014 ዓ.ም የትምህርት ዘመን 532፣ 410 እና 513 በድምሩ 1,455 (67.36%) ከደረጃ አንድ ወደ ደረጃ ሁለት ላይ አድገዋል። ይህም አፈፃፀም ከምዕራፍ አንድ 2,160 ኦ-ክፍሎች ውስጥ ትግራይ ክልል 316 ኦ-ክፍሎች ን በመቀነስ 1,844 ኦ-ክፍሎችን በዕቅድ ተይዞ ማለት ሲሆን በፕሮግራሙ የጊዜ ሰሌዳ ተይዞ ከነበረው ዕቅድ 70% በታች ሆኗል።

7.2 ምዕራፍ ሁለት ኦ ክፍሎች ኢንስፔክሽን

በ2014ዓ.ም የተከናወነ ምዕራፍ ሁለት ኦ-ክፍል የመጀመሪያ ዙር ኢንስፔክሽን በደረጃ

ሠንጠረዥ፡ 8ምዕራፍ ሁለት ኦ-ክፍል የመጀመሪያ ዙር ኢንስፔክሽን በደረጃ

ክልል	ዕቅድ	አፈፃፀም	አፈፃፀም (%)	ደረጃ-1	ደረጃ-1 (%)	ደረጃ-2	ደረጃ-2 (%)	ደረጃ-3	ደረጃ-3 (%)	ደረጃ-4	ደረጃ-4 (%)
አዲስ አበባ	61	38	62%	8	21%	29	76%	1	3%		0%
አፋር	174	120	69%	99	83%	20	17%	1	1%		0%
አማራ	2,314	1,568	68%	1,074	68%	480	31%	14	1%		0%
ቤኒሻንጉል	152	46	30%	25	54%	20	43%	1	2%		0%
ድሬዳዋ	20	20	100%	3	15%	15	75%	2	10%		0%
ጋምቤላ	64	64	100%	33	52%	29	45%	2	3%		0%
ሐረሪ	18	17	94%	3	18%	14	82%		0%		0%
ኦሮሚያ	3,580	3,109	87%	1,918	62%	1,152	37%	39	1%		0%
ሲዳማ	180	178	99%	23	13%	138	78%	17	10%		0%
ደቡብ ኢ/ሕ	1,472	940	64%	401	43%	504	54%	35	4%		0%
ሶማሌ	394	375	95%	339	90%	36	10%		0%		0%
ደቡብ ምዕራብ	231	231	100%	134	58%	86	37%	11	5%		0%
ሀገር አቀፍ	8,660	6,706	77%	4,060	61%	2,523	38%	123	2%	-	0%

ከላይ በሰንጠረዥ 9 የተመለከተው የክልሎች ምዕራፍ ሁለት ኦ-ክፍል ኢንስፔክሽን አፈፃፀም በደረጃ ያሳያል። በክልል ደረጃ ድሬዳዋ፣ ጋምቤላ፣ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ለሁለም ምዕራፍ ሁለት ኦ-ክፍሎች የኢንስፔክሽን አገልግሎት የተሰጠ ሲሆን በሌሎች ክልሎች አፈፃፀሙ ከ100% በታች ነው። በሀገር አቀፍ ደረጃ ከተያዘው ዕቅድ 8,660 ውስጥ 6,706(77%) ለሚሆኑት የኢንስፔክሽን አገልግሎት ያገኙ ሲሆኑ አፈፃፀም ደረጃቸውም 4,060 (61%) የሚሆኑት ደረጃ አንድ ፣ 2,523 (38%) የሚሆኑት ደረጃ ሁለት እና 123 (2%) የሚሆኑት ደረጃ ሶስት መሆናቸው ከተሰበሰበው መረጃ ለማወቅ ተችሏል።

በአጠቃላይ በሁለት ምዕራፍ ውጤትን መሰረት ያደረገ የኦ-ክፍል ትምህርት የኢንስፔክሽን አፈፃፀሙ በርካታ ትኩረት የሚፈልግ እንደሆነና መሻሻል የሚፈልጉ ጉዳዮች ያለበት እንደሆነ መረዳት ተችሏል። የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ለሕጻናቱ የነገ ህይወታቸው መሰረት የሚጣልበት በመሆኑ የመንግስት አካላት እና ህብርተሰቡ በቅንጅት እና ለሕፃናቱ ደህንነት የማያሰጋ ምቹ የመማሪያ አካባቢን እንዲፈጠር ማመቻቸት ይጠበቅባቸዋል።

8. መደምደሚያ

በገጠር እና በከተማ በሚገኙ የኦ-ክፍሎች መካከል የሚታየው አፈፃፀም ሲነፃፅር በከተማ ከሚገኙ ከ5.7% እስከ 6.9% የተሻለ አፈፃፀም የተመዘገበ ሲሆን በገጠር የሚገኙት ከሀገር አቀፉ አፈፃፀም እጅግ ዝቅ ብለው ይገኛሉ። በመሆኑም በሁለቱ መካከል የሚታየውን ክፍተት ከመሙላት ረገድ የትምህርት ቤት ፋሲሊቲ ህንፃዎች፣ የመማርና እንክብካቤ፣ የማስተማር፣ የሥርዓተ ትምህርት አተገባበር፣ የህፃናት ተሳትፎና የውስጥ ብቃት፣ የህፃናት ግለ-ስብዕና፣ የመምህራንና የርዕሰ መምህራን ግለ-ስብዕናን ለማሻሻል ሁሉም ባለድርሻ አካላት ትኩረት ሰጥተው እንዲሠሩ ማድረግ ይጠበቃል።

ለኦ-ክፍሎች የትምህርት ፋሲሊቲዎችና መማሪያ ክፍሎች ከማሟላት አንፃር የክልሎችን አፈጻጸም ስንመለከት ከፍተኛ ያስመዘገቡት ውጤት 61% ሲሆን ዝቅተኛው 38% መሆኑን፣ ከ10 ክልሎችና 2 ከተማ አስተዳደሮች ከትኩረት መስኮቹም አንፃር ደረጃውን ያሟላ አንድም ክልል አለመኖሩ ከላይ የቀረበው የትንተና ውጤት ያሳያል ። በተመሳሳይ የሰው ኃይል ከማቅረብ አንፃር የክልሎችን አፈጻጸም ስንመለከት ከፍተኛ 54% ሲሆን ዝቅተኛው 34% መሆኑ ሁሉም ክልሎች ለኦ- ክፍሎች የሚያስፈልገው የሰው ኃይል ከማቅረብ አንፃር ትኩረት ሰጥተው መስራት ይጠበቅባቸዋል።

ለኦ-ክፍሎች የሀብት ምንጭ ከማስፋትና ለተቋማቱ የሚያስፈልገውን በጀት ከመመደብ አንፃር የክልሎችን አፈጻጸም ስንመለከት የተመዘገበው ከፍተኛ ውጤት 53% ሲሆን ዝቅተኛው 37% ነው። በዚህ የትኩረት መስክ በቂ የፋይናንስ አቅርቦት ከማሟላት አንፃር ደረጃውን ያሟላ አንድም ክልል አለመኖሩን ከትንተና ውጤቱ መረዳት ተችሏል። ምቹ የመማሪያና ማስተማሪያ አካባቢ ከመፍጠር አንፃር የክልሎችን አፈጻጸም ስንመለከት የተመዘገበው ከፍተኛ ውጤት 51% ሲሆን ዝቅተኛው 36% ነው። መማሪያ አካባቢዎችን ለሕፃናቱ ደህንነት የማያሰጋ ምቹ የመማሪያ አካባቢን በመፍጠር ላይ በቂ ትኩረት ከመስጠት በተጨማሪም ሁሉም ክልሎች ከመማርና እንክብካቤ አንፃር ትኩረት ሰጥተው መስራት እና ከስጋት ነፃና ምቹ የመማር ማስተማር አካባቢ ከመፍጠር አንፃር ትኩረት ሰጥተው መስራት ይጠበቅባቸዋል። የሚጠበቅባቸው ሲሆን በተለይ የአፈጻጸም ውጤታቸው ከ50% በታች የሆኑ ክልሎች አሁን ያሉበትን ዝቅተኛ አፈጻጸም ለማሻሻል ልዩ ትኩረት ሰጥተው መስራት ይጠበቅባቸዋል።

ከመማር ማስተማር ዙሪያ የሀገር አቀፉ አማካይ አፈፃፀም 49% አፈፃፀም ሲታይ የሐረሪ 63% እና የአዲስ አበባ 62% የተሻለ አፈፃፀም ሲያስመዘግቡ የተቀሩትም ክልሎች ዝቅተኛ ውጤት ማስመዝገባቸው የሀገር አቀፉ አፈፃፀሙን ደረጃ አንድ ላይ እንዲወድቅ አድርጎታል። መምህራን የሕጻናቱን የዕድገት ፍላጎት፣ ፍጥነት መረዳት እና የትምህርት ዕቅድ በአግባቡ በማቀድና ለሁሉም ህፃናት ተስማሚ የማስተማር ሥነ-ዘዴዎችን በመጠቀም መተግበር ይጠበቅባቸዋል።

ሥርዓተ ትምህርቱ ተገቢነት ያለው፣ አሳታፊ እና የህፃናቱን የዕድገት ደረጃ፣ ፍላጎቶችና ልዩነት ያገናዘበ መሆኑን ከማረጋገጥ በቂ ስልጠና እና የስርዓተ ትምህርት ዝግጅት የሚጠይቅ በመሆኑ ከፍተኛ ትኩረት የሚጠይቅ ጉዳይ ነው። የኦ-ክፍሎች መምህራን የሕፃናቱን አጠቃላይ አካላዊ፣ አእምሯዊና ማህበራዊ ዕድገታቸው ላይ ክትትልና ግምገማ በማድረግ የኦ ክፍል የሥርዓተ ትምህርት አተገባበር እና የምዘና ስርዓት ውጤታማ እንዲሆን መስራት ይጠበቃል። በተለይም የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም የሁለት ዓመት በመሆኑ የመማሪያ መፃህፍት ዝግጅትና የመምህራን ልማት ላይ ተኩረት ወስዶ መስራት ያስፈልጋል። የኦ-ክፍል ትምህርትን ጥራት ለማሻሻል ወላጆች ለኦ-ክፍል የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን፣ ገንዘብ፣ ቁሳቁስ... ወዘተ በማሟላት፣ የዕውቀት እና የጉልበት ድጋፍ ማድረግ እንዲሁም የእነዚህን ትምህርት ቤቶች ደረጃ ለማሻሻል በየትምህርት ቤቶቹ በሚደራጁው የወላጆች/አሳዳጊዎች ኮሚቴ ውስጥ ተሳትፎ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።የኦ ክፍል ትምህርት የሚሰጥባቸው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ርዕሰ መምራን ወይም የኦ ክፍል አስተባባሪዎች፣ ወላጆችና የአካባቢውን ማህበረሰብ ለኦ-ክፍል ትምህርት መስጫ የባለቤትነት ስሜት እንዲጎለብት አስፈላጊውን የገንዘብ፣ የጉልበት፣ የዓይነትና የሙያ ድጋፍ በማስተባበር ማሟላት ይጠበቅባቸዋል።

የኦ-ክፍል ትምህርት ህፃናት ለቀጣይ ህይወታቸው መሰረት የሚጣልላቸውና የማህበረሰቡን ልዩ ትኩረት የሚፈልጉ እንደመሆናቸው ደረጃቸውን የማሻሻል ስራ ካልተሰራ በህፃናቱ ቀጣይ የትምህርት ዕድገት ላይ ሊያደርስ የሚችለውን አሉታዊ ተጽዕኖ ለመቀነስ ብሎም ለመቅረፍ እንዲቻል በየክልሉ ያሉና የኢንስፔክሽን አገልግሎት ያላገኙ ትምህርት ቤቶች አገልግሎቱን አግኝተው ደረጃቸውን እንዲያውቁ እንዲሁም የኢንስፔክሽን አገልግሎት አግኝተው ከደረጃ በታች የሆኑ የኦ-ክፍሎችን ደረጃ ለማሻሻል ሁሉም ባለድርሻ አካላት የድርሻቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል።

9. ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫ

የሀገራችንን የትምህርትና ስልጠና ጥራትና ደረጃ ለማሻሻል የተዘጋጀው ፍኖተ ካርታ የቅድመ አንደኛ ተደራሽንትን አስመልክቶ ከሌሎች ሀገሮች ጋር ሲነጻጸር ዝቅተኛ አፈጻጸም እንዳለን ከማመልከቱ በተጨማሪ፣ የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ሕፃናት ከ4+ - 5+ ዕድሜያቸው እንዲማሩ ማድረግ፣ ኦ-ክፍል የመደበኛ አጠቃላይ ትምህርት አካል ማድረግን እንደ ምክረሃሳብ ጠቁሟል። በቀጣይ እንደሚጸድቅ የሚጠበቀው ረቂቅ ፖሊሲም የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ነጻና አስገዳጅ መሆን እንዳለበት ይደነግጋል። ስለዚህ መንግስት የኦ-ክፍል ጨምሮ የቅድመ አንደኛ ትምህርትን የአጠቃላይ ትምህርት አካል በማድረግ፣ በየደረጃው ራሱ አስችሎ ማዋቀር ፣ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ጠቀሜታን ወላጆችና ህብረተሰቡን ማስገንዘብ፣ ከተማና ገጠርን ሳይለይ የአካበቢ ህብተሰብና አጋር ድርጅቶችን በማስተባበር ተደራሽነትና ፍትሃዊነትን ማረጋገጥ ይኖርበታል።

ኦ-ክፍሎችን ጨምሮ ሌሎች የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ተቋማት ለደረጃው የሰለጠነ አመራርና መምህርን ማግኘታቸው ለሚሰጠው የማስተማር እና እንክብካቤ ጥራት የማይተካ ሚና አለው። ስለዚህ መንግስት የአፀደ ሕጻናት አመራርና መምህራን ስልጠና ስርዓተ ትምህርት ተዘጋጅቶለት በሁሉም መምህራን ኮሌጆች እንዲሰጥ ማስፋፋት አለበት። በየደረጃው የሚገኙ የትምህርት ቢሮዎችና ጽ/ቤቶች አግባብነት ያለው በጀት በመመደብ የሰለጠኑ መምህራን፣ ረዳት መምህራን እና ሌሎች ስታንዳርዱ የሚጠይቃቸውን የሰው ሃይል ማሟላት ይኖርባቸዋል። ከዚህ በተጨማሪ አፋጣኝ መፍትሄ ለመስጠት ለኦ-ክፍል መምህራን እየተሰጠ ያለውን የአጭር ጊዜ የስራ ላይ ስልጠና ለሁሉም ተደራሽ ማድረግ ያስፈልጋል።

የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት መማሪያ አካባቢን ለሕጻናት ምቹ፣ ሳቢና ማራኪ የሚያደርገው የመማርያ ክፍሎች ፣ የመማርያና መጫዎቻ ቁሳቁስ (የመማሪያ ክፍል ውስጣዊና ውጫዊ) መሟላታቸው ነው። የኦ-ክፍሎች ትምህርት ከግማሽ በሚበልጡ ትምህርት ቤቶች በአንድ ክፍል ብቻ የሚካሄድ ተግባር ነው። ስለዚህ መንግስት ህብረተሰቡን በማስተባበር የኦ-ክፍሎችን ግንባታ ማስፋፋት ይኖርበታል። ለቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት የሚያገለግሉ ፋሲሊቲዎች በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ ማበረታታት፣ የአካባቢያቸወን ግብዓት በመጠቀም የትምህርት ፋሲሊቲዎች ለማዘጀት የሚያስችሉ ማዕከላትን ማጠናከር፣ አቅም በፈቀደ ፋሲሊቲዎችን በግዥ ማቅረብ ፤

የኢጋሮች ድጋፍ በዚህ ላይ እንዲያተኩር በማድረግ ትምህርትን በጫወታ በመማር ለቀጣይ ደረጃ የተዘጋጀ ትውልድ ለመቅረጽ ያስችላል።

ኦ-ክፍሎች ከታየባቸው የአፈጻጸም ክፍተቶች መካከል የወላጆች፣ የአካባቢ ማህብረሰብና አጋር ድርጅቶች ማንቀሳቀስና በቂ የፋይናንስና ሌሎች ግብዓት ማሟላት አለመቻል ተጠቃሽ ነው። የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርትን ጥራትና ተደራሽነት በመንግስት ወጪ ብቻ መሸፈን አይቻልም። ስለዚህ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ርእሳነ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ለመደበኛ ትምህርት ከሚያደርጉት ጥረት ባልተናነሰ መልኩ ወላጆች እና የኦ-ክፍሎች ያላቸውን ግንኙነት ማጠናከር፣ አጋር ድርጅቶች ጋር ትስስር በመፍጠር ኦ-ክፍሎች የፋይናንስና ቁሳዊ ድጋፍ እንዲያገኙ ማስቻል ይኖርባቸዋል። የአጠቃላይ ትምህርት ሴክተሩ ይህን ከመፈጸም አንጻር አስፈላጊውን የተጠያቂነት ስርዓት መዘርጋት ይኖርበታል።

በቅድመ አንደኛ የትምህርት ጥራትን የሚወስኑ አበይት ክንውኖች መካከል መማርና እንክብካቤ ቀዳሚዎቹ ናቸው። የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ፊደልና ቁጥር ከማስለየት የዘለለና ተጠንተው የተረጋገጡ በፔዳጎጂ ተቀባይነት ያላቸው ልምዶችን የሚተገብሩበት እና ሕጻናት በጫወታ ለመማር የሚያስችላቸው ስርዓተ ትምህርት ሊዘጋጅላቸው ይገባል። የህጻናቱን አካላዊ ፣ ማህበራዊ፣ ስሜታዊ ፣ የቋንቋ እና ማንበብና መጻፍ የመረዳት (Cognitive) ክህሎቶችን የሚያዳብር ስርዓተ ትምህርት መሆን አለበት። በሀገራችን የታተሙና በገበያ ላይ የሚገኙ የማስተማርያ መጻህፍት እጥረት ይስተዋላል። ስለዚህ የቅድመ አንደኛ መማርያ መጻሕፍት ህትመትን በድጎማ ዋጋ በማበርከት ማበረታታት ጠቃሚ ነው። ሕጻናት ሳይፈሩና ሰይሸማቀቁ በራስ መተማመን በማጎልበት ፣ ደህንነታቸው ተጠብቆና በፍቅር የሚማሩበት ሁኔታ እንዲጠናከር የመምህራን ተከታታይ ስልጠና የሚያገኙበት ስልት ሊዘረጋ ይገባል።

ተቀፅላ

በዚህ ሀገር አቀፍ የኢንስፔክሽን አፈፃፀም ግምገማ ሰነድ የቅድመ አንደኛ ኡ-ክፍል የሚገኝበት ሁኔታ ተተንትኖ ቢቀርብም በየደረጃው በሚገኙ አካላት ተከታታይ ድጋፍ ተደርጎላቸው ወደ ስታንዳርዱ እንዲመጡ የሁሉም ባለድርሻ አካላት ፍላጎት መሆኑ ይታወቃል። ከፌደራል ትምህርት ሚኒስቴር ጀምሮ የክልል ት/ቢሮዎች፣ የዞን ትምህርት መምሪያዎች እና የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤቶች እንዲሁም በየደረጃው የሚገኙ ባለድርሻ አካላትና የትምህርት ማህበረሰቡ ጨምሮ ከደረጃ በታች ለሆኑ የትምህርት ተቋማት ደረጃ ለማሻሻል ቀጥሎ በሚመለከታቸው ስታንዳርዶች (በግብዓት ሰድሰት እና በሂደት *አሰራ ሁለት*) መሠረት በማቀድ እገዛ ማደረግ ይጠበቅባቸዋል።

ስታንዳርዶች	የኦ-ክፍሎች ተፈላጊውን ስታንዳርድ እንዲያሟሉና አፈፃፀም ደረጃቸው እንዲሻሻል በየደረጃው የሚመለከታቸውሥራ ሂደቶች				
	ፌደራል ት/ሚኒስቴር	ክልል ት/ቢሮ	ዞን ት/መምሪያ	ወረዳ ት/ፅ/ቤት	ኦ-ክፍሎች
ስታንዳርድ 1፡- የ"ኦ" ክፍል መማሪያ ለደረጃው በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት የመገልገያ ህንፃዎች ፣ ፋሲሊቲዎች ፣ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች እና የማስፈጸሚያ ሰነዶች አሟልቷል ።	የትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል የትምህርት ዕቅድና ሀብት ማፈላለግ መሪ ስራ አስፈፃሚ፣	ክልል ት/ቢሮ፣ የትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል ፣ የትምህርት ዕቅድና ሀብት ማፈላለግ ስራ ክፍል፣	የዞን ትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል፣	ወረዳ ት/ጽቤት፣ ትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል፣	ውተመህ እና ሀብረተሰቡ
ስታንዳርድ 2፡- ለ"ኦ" ክፍል ትምህርት ለደረጃው የሚመጥን ርዕሠ-መምህር / አስተባባሪ፣ መምህራን፣ ረዳት መምህር/ት እና ሞግዚቶች በስታንዳርዱ መሰረት አሟልቷል። /	የመምህራንና የትምህርት አመራር ልማት ፣ የትምህርት ዕቅድና ሀብት ማፈላለግ መሪ ስራ አስፈፃሚ፣	ክልል ት/ቢሮ፣ የመምህራንና የትምህርት አመራር ልማት ፣ የትምህርት ዕቅድና ሀብት ማፈላለግ ስራ ክፍል፣	የዞን ትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል፣	ወረዳ ት/ጽቤት፣ ትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል፣	ውተመህ እና ሀብረተሰቡ
ስታንዳርድ 3፡- ለ"ኦ" ክፍል ትምህርት ቅድሚያ ሰጥቶ ላቀዳቸው ተግባራት ማስፈፀሚያ የሚያገለግል የፋይናንስ ሃብት ተሟልቷል።	የትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል ፣ የትምህርት ዕቅድና ሀብት ማፈላለግ መሪ ስራ አስፈፃሚ፣	ክልል ት/ቢሮ፣ የትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል ፣ የትምህርት ዕቅድና ሀብት ማፈላለግ ስራ ክፍል፣	የዞን ትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል፣	ወረዳ ት/ጽቤት፣ ትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል፣	ውተመህ እና ሀብረተሰቡ
ስታንዳርድ 4፡- ትምህርት ቤቱ ለሕጻናት ምቹ፣ የማያሰጋ እና ደህንነታቸውን የሚያረጋግጥ ሁኔታዎችን ፈጥሯል።	የትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል ፣ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ የአካባቢ ጥበቃ	የትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል መሪ፣ የክልሉ ጤና ቢሮ፣ የአካባቢ ጥበቃ ስራ ክፍል፣	የዞን ትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል፣ የዞን ጤና ጽ/ቤት፣ የዞኑ አካባቢ ጥበቃ ስራ ክፍል፣	የወረዳ ትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል፣ የወረዳ ጤና ጽ/ቤት፣ የወረዳ አካባቢ ጥበቃ ስራ ክፍል፣	ውተመህ እና ሀብረተሰቡ
ስታንዳርድ 5፡- ትምህርት ቤቱ ለ"ኦ" ክፍል ትምህርት አመታዊ ዕቅድ አዘጋጅቷል።	የትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል ፣ የትምህርት ዕቅድና ሀብት ማፈላለግ መሪ ስራ አስፈፃሚ፣	ክልል ት/ቢሮ፣ የትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል ፣ የትምህርት ዕቅድና ሀብት ማፈላለግ ስራ ክፍል፣	የዞን ትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል፣	ወረዳ ት/ጽቤት፣ ትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል፣	ውተመህ እና ሀብረተሰቡ
ስታንዳርድ 6፡- ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሰረት የክፍል	የትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል ፣ የትምህርት	የትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል ፣ የትምህርት	የትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል ፣	ወረዳ ት/ጽ/ቤትና ክላስተር ሱፐርቫይዘር	የኦ-ክፍሉ አመራር

ስታንዳርዶች	የኦ-ክፍሎች ተፈላጊውን ስታንዳርድ እንዲያሟሉና አፈፃፀም ደረጃቸው እንዲሻሻል በየደረጃው የሚመለከታቸውሥራ ሂደቶች				
	ፌደራል ት/ሚኒስቴር	ክልል ት/ቢሮ	ዞን ት/መምሪያ	ወረዳ ት/ፅ/ቤት	ኦ-ክፍሎች
ውጪ የመጫወቻ መሣሪያዎችና ምቹ የመሬት ወለል አሉት።	ዕቅድና ሀብት ማፈላለግ መሪ ስራ አስፈፃሚ፣	ዕቅድና ሀብት ማፈላለግ መሪ ስራ አስፈፃሚ፣	የትምህርት ዕቅድና ሀብት ማፈላለግ		
ስታንዳርድ 7፡- ሕጻናት ተገቢውን እንክብካቤ አግኝተዋል።	የመምህራንና የትምህርት አመራር ልማት ፣ የትምህርት ዕቅድና ሀብት ማፈላለግ ስራ ክፍል፣	የመምህራንና የትምህርት አመራር ልማት ፣ የትምህርት ዕቅድና ሀብት ማፈላለግ ስራ ክፍል፣	የመምህራንና የትምህርት አመራር ልማት ፣ የትምህርት ዕቅድና ሀብት ማፈላለግ ስራ ክፍል፣	ክላስተር ሱፐርቫይዘር	የኦ-ክፍሉ አመራር
ስታንዳርድ 8:- የትምህርት ቤቱ ህፃናት ተገቢውን ጥበቃ አግኝተዋል፡	የትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል መሪ ስራ አስፈፃሚ፣	የትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል ፣ የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ቢሮ	የትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል ፣ የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጽ/ቤት	የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጽ/ቤት	የኦ-ክፍሉ አመራርና
ስታንዳርድ 9 ፡- መምህራን የሕጻናቱን የእድገት ፍላጎት፣ ፍጥነትና ልዩነት ያገናዘበ የእንክብካቤና የትምህርት ዕቅድ በማቀድ ተግባራዊ አድርገዋል ።	የትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል መሪ ስራ አስፈፃሚ፣ ልዩ ድጋፍና አካታች ትምህርት፣የትምህርት ዕቅድና ሀብት ማፈላለግ ስራ ክፍል፣	የትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል መሪ ስራ አስፈፃሚ፣ ልዩ ድጋፍና አካታች ትምህርት፣ የትምህርት ዕቅድና ሀብት ማፈላለግ ስራ ክፍል፣	የትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል መሪ ስራ አስፈፃሚ፣	የትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል ፣ ልዩ ድጋፍና አካታች ትምህርት፣	የኦ-ክፍሎች
ስታንዳርድ 10፡- መምህራንና ረዳት መምህራን ሕጻናትን የመንከባከብ ዘዴ እና የትምህርቱን ይዘት ጠንቅቀው ያውቃሉ	የትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል መሪ ስራ አስፈፃሚ፣ ልዩ ድጋፍና አካታች ትምህርት፣የትምህርት ዕቅድና ሀብት ማፈላለግ ስራ ክፍል፣	የትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል መሪ ስራ አስፈፃሚ፣ ልዩ ድጋፍና አካታች ትምህርት፣ የትምህርት ዕቅድና ሀብት ማፈላለግ ስራ ክፍል፣	መምህራን ትምህርት አመራርና ልማት ስ/ሂደት	መምህራን ትምህርት አመራርና ልማት ስ/ሂደትና ክላስተር ሱፐርቫይዘር	የኦ-ክፍሉ አመራርና ሱፐርቫይዘር ኮሚቴ፣

ስታንዳርዶች	የኦ-ክፍሎች ተፈላጊውን ስታንዳርድ እንዲያሟሉና አፈፃፀም ደረጃቸው እንዲሻሻል በየደረጃው የሚመለከታቸውሥራ ሂደቶች				
	ፌደራል ት/ሚኒስቴር	ክልል ት/ቢሮ	ዞን ት/መምሪያ	ወረዳ ት/ፅ/ቤት	ኦ-ክፍሎች
ስታንዳርድ 11 ፡- የ"ኦ" ክፍል ርዕሰ መምህር/አስተባባሪ ፣ መምህራንና ረዳት መምህራን ለሁሉም ህፃናት ተስማሚና ህፃን ተኮር የማስተማር እና የእንክብካቤ ስነ-ዘዴዎችን በመጠቀማቸው የሁሉም ህፃናት ንቁ ተሳትፎ አድጓል ።	የመምህራንና የትምህርት አመራር ልማት ፣ የትምህርት ዕቅድና ሀብት ማፈላለግ ስራ ክፍል፣	የመምህራንና የትምህርት አመራር ልማት ፣ የትምህርት ዕቅድና ሀብት ማፈላለግ ስራ ክፍል፣	የመምህራንና የትምህርት አመራር ልማት ፣ የትምህርት ዕቅድና ሀብት ማፈላለግ ስራ ክፍል፣	የመምህራንና የትምህርት አመራር ልማት ፣ የትምህርት ዕቅድና ሀብት ማፈላለግ ስራ ክፍል፣	የኦ-ክፍሉ አመራርና ሱፐርቫይዘር
ስታንዳርድ12፡- "ኦ" ክፍል ትምህርትን በተመለከተ ትምህርት ቤቱ አግባብነት ያለው የሰው፣ የገንዘብ እና የንብረት ሃብት አጠቃቀም ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አድርጓል።	የትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል መሪ ስራ አስፈፃሚ፣ ልዩ ድጋፍና አካታች ትምህርት፣ የትምህርት ዕቅድና ሀብት ማፈላለግ ስራ ክፍል፣	የትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል ፣ ልዩ ድጋፍና አካታች ትምህርት፣ የትምህርት ዕቅድና ሀብት ማፈላለግ ስራ ክፍል፣	የትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል ፣ ልዩ ድጋፍና አካታች ትምህርት፣ የትምህርት ዕቅድና ሀብት ማፈላለግ ስራ ክፍል፣	የትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል ፣ ልዩ ድጋፍና አካታች ትምህርት፣ የትምህርት ዕቅድና ሀብት ማፈላለግ ስራ ክፍል፣	የኦ-ክፍሉ አመራርና ሱፐርቫይዘር
ስታንዳርድ 13 ፡- በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብና በህፃናት መካከል በመፈቃቀር፣ በመከባበርና በመተሳሰብ ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ተፈጥሯል።	የትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል መሪ ስራ አስፈፃሚ፣ ልዩ ድጋፍና አካታች ትምህርት፣ የትምህርት ዕቅድና ሀብት ማፈላለግ ስራ ክፍል፣	የትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል ፣ ልዩ ድጋፍና አካታች ትምህርት፣ የትምህርት ዕቅድና ሀብት ማፈላለግ ስራ ክፍል፣	የትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል ፣ ልዩ ድጋፍና አካታች ትምህርት፣ የትምህርት ዕቅድና ሀብት ማፈላለግ ስራ ክፍል፣	የትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል ፣ ልዩ ድጋፍና አካታች ትምህርት፣ የትምህርት ዕቅድና ሀብት ማፈላለግ ስራ ክፍል፣	የኦ-ክፍሉ አመራርና ሱፐርቫይዘር

ስታንዳርዶች	የኦ-ክፍሎች ተፈላጊውን ስታንዳርድ እንዲያሟሉና አፈፃፀም ደረጃቸው እንዲሻሻል በየደረጃው የሚመለከታቸውሥራ ሂደቶች				
	ፌደራል ት/ሚኒስቴር	ክልል ት/ቢሮ	ዞን ት/መምሪያ	ወረዳ ት/ፅ/ቤት	ኦ-ክፍሎች
ስታንዳርድ 14 ፡- ትምህርት ቤቱ ልዩ ፍላጎት ያላቸው የ"አ" ክፍል ህፃናትን የተመለከቱ መረጃዎችን ይሟል፣ ልዩ ድጋፍም አድርጓል።	*የትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል መሪ ሰራ አስፈፃሚ፣ ልዩ ድጋፍና አካታቶ ትምህርት፣ የትምህርት አስተዳደርና መረጃ አቅርቦት፣*	*የትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል መሪ ሰራ አስፈፃሚ፣ ልዩ ድጋፍና አካታቶ ትምህርት፣ የትምህርት አስተዳደርና መረጃ አቅርቦት፣*	*የትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል መሪ ሰራ አስፈፃሚ፣ ልዩ ድጋፍና አካታቶ ትምህርት፣ የትምህርት አስተዳደርና መረጃ አቅርቦት፣*	*የትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል መሪ ሰራ አስፈፃሚ፣ ልዩ ድጋፍና አካታቶ ትምህርት፣ የትምህርት አስተዳደርና መረጃ አቅርቦት፣*	*የኦ-ክፍሉ አመራርና ሱፐርቫይዘር*
ስታንዳርድ 15፡- የ"አ" ክፍል መምህራን፣ ረዳት መምህራን እና ሞግዚቶች በቡድን ስሜት እየሰሩ ነው።	*የመምህራንና የትምህርት አመራር ልማት ፣ የትምህርት ፅቅድና ሀብት ማፈላለግ ሰራ ክፍል፣*	*የመምህራንና የትምህርት አመራር ልማት ፣ የትምህርት ፅቅድና ሀብት ማፈላለግ ሰራ ክፍል፣*	*የመምህራንና የትምህርት አመራር ልማት ፣ የትምህርት ፅቅድና ሀብት ማፈላለግ ሰራ ክፍል፣*	*የመምህራንና የትምህርት አመራር ልማት ፣ የትምህርት ፅቅድና ሀብት ማፈላለግ ሰራ ክፍል፣*	*የኦ-ክፍሉ አመራርና ሱፐርቫይዘር*
ስታንዳርድ 16 ፡- ሥርዓተ ትምህርቱ ተገቢነት ያለው፣ አሳታፊ እና የህፃናቱን የእድገት ደረጃ፣ ፍላጎቶችና ልዩነት ያገናዘበ ነው።	*የመምህራንና የትምህርት አመራር ልማት ፣ የሥርዓተ ትምህርት ዝግጅትና ትግበራ፣*	*የመምህራንና የትምህርት አመራር ልማት ፣ የሥርዓተ ትምህርት ዝግጅትና ትግበራ፣*	*የመምህራንና የትምህርት አመራር ልማት ፣ የሥርዓተ ትምህርት ዝግጅትና ትግበራ፣*	*የመምህራንና የትምህርት አመራር ልማት ፣ የሥርዓተ ትምህርት ዝግጅትና ትግበራ፣*	*የኦ-ክፍሉ አመራርና ሱፐርቫይዘር*
ስታንዳርድ 17፡- ህፃናት በአካል፣ በአእምሮ፣ በስሜትና በማህበራዊ እድገታቸው የሚያሳዩት መሻሻል በማህደረ ተግባር /ፖርትፎልዮ/ ተመዝግቧል።	*የመምህራንና የትምህርት አመራር ልማት ፣ የሥርዓተ ትምህርት ዝግጅትና ትግበራ፣*	*የመምህራንና የትምህርት አመራር ልማት ፣ የሥርዓተ ትምህርት ዝግጅትና ትግበራ፣*	*የመምህራንና የትምህርት አመራር ልማት ፣ የሥርዓተ ትምህርት ዝግጅትና ትግበራ፣*	*የመምህራንና የትምህርት አመራር ልማት ፣ የሥርዓተ ትምህርት ዝግጅትና ትግበራ፣*	*የኦ-ክፍሉ አመራርና ሱፐርቫይዘር*
ስታንዳርድ 18 ፡- ትምህርት ቤቱ ከህፃናት ወላጆች/አሳዳጊዎችና	*የትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል መሪ ሰራ*	*የትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል ፣ ልዩ ድጋፍና*	*የትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል ፣*	*የትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት ማሻሻል*	*የኦ-ክፍሉ አመራርና ሱፐርቫይዘር*

ስታንዳርዶች	የኦ-ክፍሎች ተፈላጊውን ስታንዳርድ እንዲያሟሉና አፈፃፀም ደረጃቸው እንዲሻሻል በየደረጃው የሚመለከታቸውሥራ ሂደቶች				
	ፌደራል ት/ሚኒስቴር	ክልል ት/ቢሮ	ዞን ት/መምሪያ	ወረዳ ት/ፅ/ቤት	ኦ-ክፍሎች
ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ጠንካራ ግንኙነት አለው።	አሰፈፃሚ፣ ልዩ ድጋፍና አካተዱ ትምህርት፣ የትምህርት ዕቅድና ሀብት ማፈላለግ ስራ ክፍል፣	አካተዱ ትምህርት፣ የትምህርት ዕቅድና ሀብት ማፈላለግ ስራ ክፍል፣	ልዩ ድጋፍና አካተዱ ትምህርት፣ የትምህርት ዕቅድና ሀብት ማፈላለግ ስራ ክፍል፣	፣ ልዩ ድጋፍና አካተዱ ትምህርት፣ የትምህርት ዕቅድና ሀብት ማፈላለግ ስራ ክፍል፣	

